<u>አዋጅ ቁጥር194/2015</u>

# የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ጥብቅና አገልግሎት ፍቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣ አዋጅ ቁጥር 194/2015

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የጥብቅና አገልግሎት ተጠቃሚዎችን መብት በተሻለ ሁኔታ ማስከበር፣ ጥራቱን የጠበቀና የተደራጀ የጥብቅና አገልግሎት አቅርቦት መኖር፣ እና የጥብቅና አገልግሎት የሥነ-ምግባር ደረጃን ማሳደግ የሕግ የበላይነትና ፍትህ የማግኘት መብትን ለማስከበር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የጥብቅና አገልግሎት ተጠቃሚዎች እና የጠበቆችን መብት በተሻለ ሁኔታ ለማስከበር፤ የጥብቅና ሙያ አገልግሎት በአንድ አገር የፍትሕ ሥርዓት ዉስጥ ያለዉን የጎላ ሚና እና የሚያስፈልገዉን የሙያ ነጻነት ከግምት ዉስጥ በማስገባት እንዲሁም አገራችን የደረሰችበትን የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ዕድገት ታሳቢ ያደረገ የመንግስትና የባለሙያዉን ተዋፅኦ ያማከለ የጋራ አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፡

የህዝብ ጥቅምን በማስጠበቅና ፍትህን በማስፈን ዙርያ የተደራጀ፤ የመንግስትና የሙያተኞችን ተዋጽኦ ያማከለ የጋራ አስተዳደር ሥርዓት በመዘርጋት የሙያ ነጻነቱ የተጠበቀ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የጥብቅና አገልግሎት ተጠቃሚዎች ቀጣይነትና ድርጅታዊ ዋስትና ያለው የጥብቅና አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችል የጥብቅና ድርጅት የሚመራበትንና የሚተዳደርበትን ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የክልሉ የጥብቅና ፈቃድ የተሰጣቸው ጠበቆች በተከታታይ ሥልጠና አማካኝነት በየጊዜው ከሚወጡ የክልሉ እና የፌዴራሉ አዳዲስ ህጎች፣ የህግ ጽንሰ ሀሳቦች እና ክልላዊ፣ አገር አቀፍ እና አለም አቀፍ ተሞክሮዎች ጋር የሚተዋወቁበትን ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ሕገ-መንግስት አንቀፅ 49 (3.1) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፤

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ፣

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ “የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የጥብቅና አገልግሎት ፍቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር ለመወሰን ተሻሽሎ የወጣ አዋጅ ቁጥር 194/2015" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2.ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. “ክልል” ማለት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ነው፤
2. “መንግስት” ማለት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ነው፤
3. “ቢሮ” ማለት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ፍትህ ቢሮ ነው፤
4. “ጠበቃ” ማለት የግል የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት በዚህ አዋጅ መሠረት ፍቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤
5. “ማኀበር” ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 57 መሠረት የተቋቋመ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የጠበቆች ማኀበር ነው፤
6. “የጥብቅና ድርጅት” ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋመና የጥብቅና ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት ነው፤
7. “የጥብቅና ሙያ አገልግሎት” ማለት የገንዘብ ክፍያ በመቀበል ወይም ወደፊት የሚገኝ ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ሲባል ወይም ያለክፍያ በጠበቃ ወይም በጥብቅና ድርጅት የሚሰጥ ማንኛውም የሕግ አገልግሎት ሲሆን የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-
    1. በሕግ ጉዳዮች ላይ ምክር መስጠት፤ ከወንጀል ጉዳዮች ዉጪ የማደራደር ስራ፣
    2. የሕግ ሰነድ ማዘጋጀት ወይም በደንበኛው ስም ሰነድን ማቅረብ፣
    3. በፍርድ ቤቶች፣ አስተዳደራዊ ጉባዔዎች፣ ከፊል የዳኝነት ስልጣን ባላቸዉ አካላት፤ በግልግል ዳኝነት ጉባዔዎች እና በሌሎች አማራጭ የሙግት መፍቻ መድረኮች ደንበኛን ወክሎ መቅረብ እና መከራከር፡፡
8. “ደንበኛ” ማለት የጥብቅና አገልግሎት ተቀባይ ሰው ነው፤
9. “መዝገብ” ማለት በፍትህ ቢሮው የሚዘጋጅና የጥብቅና ፍቃድ የተሰጣቸው ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች ሙሉ መረጃ የሚመዘገብበት ባህር መዝገብ ወይም የመረጃ ቋት ነው፤

10."የፀና የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ፈቃድ" ማለት በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን መስፈርቶች ላሟላ ሰው የሚሰጥ ፈቃድ ነው፤

11."የታክስ ክሊራንስ" ማለት አንድ የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ፈቃድ ያለው ሰው ላገኘው ገቢ ግብር ስለመክፈሉ ከግብር አስገቢው አካል የሚሰጥ ማስረጃ ነው፡፡

12. "አገናኝ" ማለት የጥብቅና አገልግሎትን በሚመለከት ጠበቃን ወይም የጥብቅና ድርጅትን እና ባለጉዳይን በማገናኘት ከአንዱ ወይም ከሁለቱም ወገን ክፍያ ወይም ኮሚሽን በመቀበል ወይም ወደፊት ለመቀበል በማሰብ ባለጉዳዩን በማግባባትና በማሳመን ባለጉዳዩ እርሱ የመረጠለትን ጠበቃ እንዲይዝ የሚያደርግ ወይም የሚያግባባ ማንኛውም ሰው ነው፤

13."የጥብቅና ስራን በአገናኝ አማካኝነት መስራት" ማለት በፍርድ ቤቶች፣ በማረሚያ ቤቶች፣ በፖሊስ ጣቢያዎች፣ በሌሎች የፍትህ ተቋማት ወይም በማንኛውም ስፍራ ደላሎችን በማሰማራት ወይም በተሰማሩ ደላሎች ወይም ከየፍትህ ተቋማቱ ሀላፊዎች ወይም ሰራተኞች ጋር የጥቅም ትስስር በመፍጠር የጥብቅና አገልግሎት ፈላጊዎች ወደ ጠበቃው ወይም የጥብቅና ድርጅቱ እንዲመጡ የማድረግ ተግባር ነው፤

14."ነጻ የጥብቅና አገልግሎት" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 31(1) ስር ለተዘረዘሩት የጥብቅና አገልግሎት ፈላጊዎች እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ህጎች ለተመለከቱ ሰዎች በአነስተኛ ክፍያ ወይም ያለምንም ክፍያ በጠበቃ ወይም በጥብቅና ድርጅት የሚሰጥ የጥብቅና አገልግሎት ነው፤

15."የህግ ጉዳይ ጸሀፊ" ማለት በጠበቃ ወይም ጥብቅና ድርጅት ስር በመሆን በጠበቃ በኩል የሚቀርቡ ክሶችን፣ ማመልከቻዎችን፣ ይግባኞችን፣ አቤቱታዎችን፣ መልሶችን እና ሌሎች ህግ ነክ ሰነዶችን በማዘጋጀት ወይም በማረም ጠበቃን የሚያግዝ ሰው ነው፤

16."የግል የህግ ጉዳይ ፀሀፊ" ማለት ማመልከቻ ወይም የተለያዩ ዉሎችን በማዘጋጀት ለደንበኛ በክፍያ አገልግሎት የሚሰጥና በዚህ አዋጅ መሰረት በፍትህ ቢሮ የሰነዶች የጠበቆችና ማህበራት ዳይሬክቶሬትና በየደረጃዉ ባሉ የዞን ፍትህ መምሪያ የሰነዶች የጠበቆችና ማህበራት የስራ ክፍል የተመዘገበ ሰዉ ነዉ፡፡

17."የጠበቃ ረዳት" ማለት በጠበቃ ወይም ጥብቅና ድርጅት ስር በመሆን ጠበቃን የሚያማክር፣ ለጠበቃው የህግ አስተያየት የሚያዘጋጅ፣የተዘጋጁ ክሶችን፣ ማመልከቻዎችን፣ ይግባኞችን፣ አቤቱታዎችን ወይም መልሶችን ፍርድ ቤት ወይም በሌላ የህግ ሰውነት ባለው ተቋም ዘንድ በመገኘት የሚያቀርብ፤ለሚመለከተው አካል

የሚያደርስ፣ የክስ ወይም የይግባኝ መዝገብ የሚያስከፍት፤ መጥሪያዎችን፣ የውሳኔ ግልባጮችን እና ሌሎች ለጠበቃው መድረስ ያለባቸውን ሰነዶች ከሚመለከተው አካል በመቀበል ለጠበቃው የሚያደርስ ሰው ነዉ፤

18. "የሥነ ምግባር ደንብ" ማለት የጠበቆች እና ጥብቅና ድርጅቶች ሥነ-ምግባርን አስመልክቶ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣ ደንብ ነው፤
19. "ስልጠና" ማለት በዚህ አዋጅ መስረት በማህበሩ ወይም ማህበሩ እውቅና በሰጠው ተቋም አማካኝነት ለጠበቆች በስራ ላይ እያሉ የሚሰጥ የህግ ስልጠና ነዉ፤
20. "ተቋም" ማለት ተከታታይ የህግ ስልጠና የሚሰጥ ድርጅት/ ተቋም/ ነዉ፤
21. "ቦርድ" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 68(1) መሠረት የተቋቋመ የጠበቆች አስተዳደር ቦርድ ነው፤
22. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰዉ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
23. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ያካትታል።

### 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በክልሉ ፍትህ ቢሮ የጥብቅና ፈቃድ በተሰጠው ጠበቃ እና የጥብቅና ድርጅት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ስለ ፍቃድ አሰጣጥ፤ ምዝገባ እና እድሳት

### ንዑስ ክፍል አንድ

### ስለ ፍቃድ አሰጣጥ

### 4. የጥብቅና ፍቃድ መርሆዎች

1. ማንኛዉም ሰዉ ፍቃድ ሳይኖረዉ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት አይችልም፤
2. የጥብቅና ፍቃድ ቋሚ ሥራ ላለው ሰው አይሰጥም፡፡
3. ማንኛዉም የጥብቅና ፍቃድ ማግኘት የሚፈልግ ሰዉ በዚህ አዋጅ የተደነገጉ መስፈርቶችን ማሟላት አለበት፤
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እንደተጠበቀ ሆኖ ማንም ሰዉ በጾታ፤ በሀይማኖት፤ በቋንቋ፤ በዘር ወይም በማህበራዊ አመጣጡ፤በፖለቲካ አመለካከቱ፤ በንብረቱ፤ በትዉልዱ፤ በአካል ጉዳት ወይም ማንኛዉንም ተመሳሳይ ሁኔታ መሰረት በማድረግ ፍቃድ አይከለከልም፡፡

## 5. ፍቃድ የማያስፈልግበት ሁኔታ

የሚከተሉት አካላት የጥብቅና ፍቃድ ሳያስፈልጋቸዉ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት ይችላሉ፡-

1. ስለራሱ ጉዳይ የሚከራከር ሰዉ፤
2. ያለክፍያ ለትዳር ጓደኛዉ፤ ለወላጁ፤ ለልጁ፤ ለአያቱ፤ ለእህቱ፤ ለወንድሙ፤ ለትዳር ጓደኛዉ ወላጆች፤ እንዲሁም ሞግዚት ወይም አሳዳሪ ለሆነለት ሰዉ የሚከራከር ሰዉ፣
3. ከስራዉ ጋር በተያያዘ ጉዳይ የሚከራከር ዐቃቤ ህግ፣
4. ሕጋዊ ሰውነት ባለው የንግድ ድርጅት፣የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት፤ሕዝባዊ ድርጅት፣ የሃይማኖት ተቋም፣ የሙያ ማህበር፣ አለም አቀፍ ድርጅት ወይም በሌላ አግባብነት ባለዉ ህግ መሰረት በተቋቋመ ድርጅት ተቀጥሮ የተወከለ ሰው፤
5. የመንግስት መስሪያ ቤትን ወይም የልማት ድርጅትን በሚመለከት የሚከራከር ማንኛዉም የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም የልማት ድርጅት ባለስልጣን ወይም ሀላፊ ወይም በእርሱ የተወከለ ሰዉ፣ ወይምማንኛዉም የሰራተኛ ማህበር መሪ ወይም ማህበሩ የሚወክለዉ ሰዉ ፈቃድ አያስፈልገዉም

## 6. ፍቃድ ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

1. ማንኛዉም በጥብቅና ሙያ መሰማራት የሚፈልግ ሰዉ የጥብቅና ፍቃድ ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡-

   ሀ) የኢትዮጵያ ዜግነት ያለዉ ወይም ትዉልደ ኢትዮጵያዊ የሆነ፣

   ለ) ዕውቅና ካለዉ የኢትዮጵያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ቢያንስ በህግ ዲፕሎማ ያለዉ፣

   ሐ) ለመጨረሻ ጊዜ ይሰራበት ከነበረበት ተቋም ድርጅቱን ከመልቀቁ በፊት ባሉት ሁለት አመታት ዉስጥ በከባድ ዲስፕሊን ጥፋት ያልተቀጣ እና የመልካም ስነምግባር ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል፣

   መ) በህግ ሙያ የሚፈለገዉን የስራ ልምድ ያሟላ እና እንደአስፈላጊነቱ ፍቃድ ለማግኘት የሚሰጠዉን የሙያ መግቢያ ፈተና ያለፈ፤ እና

   ሠ/ የክልሉን የሥራ ቋንቋ መናገር የሚችል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ለ) የተመለከተዉ ቢኖርም ከኢትዮጵያ ዉጪ ካለ ዕዉቅና ካለዉ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም በህግ የመጀመርያ ዲግሪ የተሰጠዉ ማንኛዉም ሰዉ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13(2) እና 14(2) ስር የተመለከቱትን መስፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ የጥብቅና ፍቃድ ሊሰጠዉ ይችላል

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከቱትን መስፈርቶች የሚያሟላ ማንኛውም ሰው አስፈላጊ ሰነዶችን በማያያዝ የጥብቅና ፍቃድ ማመልከቻውን ለክልሉ ፍትህ ቢሮ ማቅረብ ይኖርበታል፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(መ) መሰረት የሚቀርበዉ የፈተና ውጤት ዋጋ የሚኖረዉ ውጤቱ በታወቀ በአንድ አመት ጊዜ ዉስጥ ከቀረበ ብቻ ነዉ፡፡

**7. ፍቃድ የማያሰጡ ምክንያቶች**

ማንኛዉም ሰዉ የጥብቅና ፍቃድ የማይሰጠው፡-

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከቱትን መስፈርቶች ያላሟላ ከሆነ፤
2. ታስቦ በሚፈፀምና ከሙያ ስነምግባር ጉድለት ጋር በተያያዘ ሶስት ዓመትና ከዚያ በላይ ጽኑ እስራት በሚያስቀጣ ወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ ከተባለ እና አግባብነት ባለው ህግ ያልተሰየመ ከሆነ፤
3. በሕግ አገለግሎት እንዳይሰማራ በሕግ ወይም በፍርድ ቤት የተከለከለ ከሆነ ነው፡፡

8. **ፍቃድ ስለመስጠት**

1. በዚህ አዋጅ መሰረት የክልል የጥብቅና ፍቃድ የሚሰጠዉ በጥብቅና ፍቃድ ገምጋሚ ኮሚቴ ዉሳኔ መሰረት በፍትህ ቢሮ ነዉ፤
2. አመልካቹ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6(3) መሰረት የተሟላ ማመልከቻ ባቀረበ በ30 ቀናት ዉስጥ የጥብቅና ፍቃድ ገምጋሚ ኮሚቴ ተገቢ የሚለዉን ዉሳኔ መስጠት አለበት፤
3. የጥብቅና ፍቃድ ማመልከቻ ተቀባይነት ካላገኘ የጥብቅና ፈቃድ ገምጋሚ ኮሚቴዉን ዉሳኔ መሰረት በማድረግ ፍትህ ቢሮው ማመልከቻው ተቀባይነት ያላገኘበትን ምክንያት የኮሚቴዉን ዉሳኔ ባወቀ በ10 የስራ ቀናት ዉስጥ በጽሁፍ ለአመልካቹ ማሳወቅ አለበት፤
4. የጥብቅና ፍቃድ ገምጋሚ ኮሚቴ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ፍቃድ እንዲሰጥ ከወሰነ በ15 የስራ ቀናት ዉስጥ የጥብቅና ፍቃዱን ለአመልካቹ በፍትህ ቢሮ በኩል መስጠት አለበት፤
5. የጥብቅና አገልግሎት ፍቃድ በሚሰጥበት ጊዜ በፍቃድ ደብተር ላይ መጠቀስ ያለባቸዉ ነጥቦች ዝርዝር ፍትህ ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፤
6. የጥብቅና ፍቃድ ገምጋሚ ኮሚቴዉ ማመልከቻዉን ዉድቅ ካደረገዉ አመልካቹ ማመልከቻው ውድቅ መደረጉን ካወቀበት ጊዜ አንስቶ በ15 የስራ ቀናት ዉስጥ ቅሬታዉን ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል፤

7. በቦርዱ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ያለዉ ወገን የውሳኔ ግልባጭ ከደረሰዉ ጊዜ ጀምሮ ባለ 30 ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

9. **ቃለ መሀላ ስለማስፈጸም**

የቃለ መሀላ ፈጻሚዉን ዕምነት ለማስተናገድ ሊደረጉ የሚችሉ ምክንያታዊ ለውጦች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛዉም የጥብቅና አገልግሎት ፍቃድ የሚሰጠዉ ጠበቃ የሚከተለዉን ቃለ መሀላ በጽሁፍ ያረጋግጣል፡-

«እኔ ………ዛሬ ……ቀን……….ዓ.ም ከ----ክልል የጥብቅና ፈቃድ ስቀበል የክልሉንና የሀገሪቱን ህገ-መንግስት እና ህጎች ላከብር እና ላስከብር፤ ለፍትህ ስርዓቱ ተልዕኮ መሳካት በመልካም ስነ-ምግባር፤ በሙያዬ በቅንነት እና በታማኝነት በመስራት የምወክላቸዉን ደንበኞቼን ጥቅም ህግ በሚፈቅደዉ አግባብ ላስከብር፤ ከተከራካሪዎቼ እና የሙያ ባልደረቦቼ ጋር በመግባባት እና በመከባበር ልሰራ እና ባለኝ እዉቀት እና ችሎታ ለህግ የበላይነት ተገቢዉን ዕገዛ ለማድረግ ቃል እገባለሁ»የሚል ሲሆን ይህም ከማህደሩ ጋር ተያይዞ የሚቀመጥ ይሆናል፡፡

10. **የጥብቅና ፍቃድ አይነቶች**

የጥብቅና ፈቃድ ዓይነቶች፡-

1. የወረዳ ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ፣
2. የማናቸውም ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ፣ እና
3. ልዩ ጥብቅና ፈቃድ፤ ናቸው፡፡

11. **የወረዳ ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ፣**

1. ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ የሆነ፤
2. በሕግ ዲፕሎማ የተመረቀና ቢያንስ ለወንድ ስምንት ለሴት ስድስት ዓመት ያገለገለ/ች፣ በህግ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለዉ እና በሙያዉ ቢያንስ ለወንድ አራት አመት ለሴት ሶስት ዓመት ያገለገለ/ች ወይም በህግ የማስትሬት ድግሪ ያለዉና በሙያዉ ሁለት ዓመት ያገለገለ/ች ወይም በህግ የዶክትሬት ድግሪ ያለዉና በሙያዉ ቢያንስ አንድ ዓመት ያገለገለ/ች፤
3. ለመጨረሻ ጊዜ ይሰራበት ከነበረበት ተቋም ድርጅቱን ከለቀቀበት ጊዜ በፊት ባሉት ሁለት አመታት ዉስጥ በከባድ ዲስፕሊን ጥፋት ያልተቀጣ፣ እና
4. መልካም ስነ-ምግባር ያለዉ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል፡፡

12. **የማናቸውም ፍርድ ቤት የጥብቅና ፈቃድ**

1. ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ የሆነ፤

2. በሕግ ዲፕሎማ የተመረቀና ቢያንስ ለወንድ ስድስት ዓመት ለሴት አምስት ዓመት ያገለገለ/ች፣ በህግ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለዉ እና በሙያዉ ቢያንስ ለወንድ ሶስት አመት ለሴት አራት ዓመት ያገለገለ/ች ወይም በህግ የማስትሬት ድግሪ ያለዉና በሙያዉ ለወንድ ሁለት ዓመት ለሴት አንድ ዓመት ያገለገለ/ች ወይም በህግ የዶክትሬት ድግሪ ያለዉና በሙያዉ ቢያንስ አንድ ዓመት ያገለገለ/ች፤
3. እንደ አስፈላጊነቱ ለደረጃው የሚሰጠውን የጥብቅና ፍቃድ መግቢያ ፈተና ያለፈ፣
4. ለመጨረሻ ጊዜ ይሰራበት ከነበረበት ተቋም ድርጅቱን ከለቀቀበት ጊዜ በፊት ባሉት ሁለት አመታት ዉስጥ በከባድ ዲስፕሊን ጥፋት ያልተቀጣ፣ እና
5. መልካም ስነ-ምግባር ያለዉ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል፡፡

13. **ልዩ የጥብቅና ፍቃድ**

በክልሉ ዉስጥ የሕብረተሰቡን አጠቃላይ መብትና ጥቅም ለማስከበር በነጻ የህግ አገልግሎት ለሚሰጥና የሚከተሉትን መስፈርቶች ለሚያሟላ ሰው የሚሰጥ ፈቃድ ነዉ፡፡

1. ኢትዮጵያዊ ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ የሆነ፤
2. በሕግ ዲፕሎማ የተመረቀና ቢያንስ ለወንድ ስድስት ለሴት አምስት ዓመት ያገለገለ/ች፣ በህግ የመጀመርያ ዲግሪ ያለዉ እና በሙያዉ ቢያንስ ለወንድ አራት ለሴት አመት ያገለገለ/ች ወይም በህግ የማስትሬት ድግሪ ያለዉና በሙያዉ ሁለት ዓመት ያገለገለ ወይም በህግ የዶክትሬት ድግሪ ያለዉና በሙያዉ ቢያንስ አንድ ዓመት ያገለገለ፤
3. ከተቋም፤ከድርጅት ወይም ከሚወክለዉ ህብረተሰብ ወይም ደንበኛ ክፍያ የማይቀበል፤
4. መልካም ስነ-ምግባር ያለዉ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ህጋዊ ከሆነና ማስረጃዉን ለመስጠት የህግ መሰረት ካለዉ አካል/ተቋም የተሰጠ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፡፡
5. ማንኛዉም የክልሉ ጥብቅና ፍቃድ ያለዉ ሰዉ ልዩ የጥብቅና ፍቃድ ሳያስፈልገዉ የልዩ ጥብቅና አገልግሎት መስጠት ይችላል፤ ነገር ግን ይህን አገልግሎት ከመስጠቱ በፊት ለፍትህ ቢሮ በጽሁፍ በማሳወቅ ይሁንታ ማግኘት አለበት፤
6. ልዩ የጥብቅና ፍቃድ የተሰጠዉ ሰዉ ወይም ድርጅት የጥብቅና አገልግሎቱን ሲሰጥ ይህን አዋጅ እና የጠበቃ ስነ-ምግባር ደንብን በተከተለ መልኩ መፈጸም አለበት፡፡

14. **ለሕግ መምህራን ስለሚሰጥ የጥብቅና ፍቃድ**

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሕግ ትምህርት ቤቶች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15 (2) ካሟላ

የህግ መምህርነት ሙያውን መልቀቅ ሳያስፈልገው የጥብቅና ፍቃድ ሊሰጠዉ ይችላል፤

2. ፈቃዱ ሲሰጥ ግን የጥብቅና ሥራው የመማር ማስተማር ሂደቱን የማያስተጓጉል ስለመሆኑ ከሚያስተምርበት ተቋም የህግ ትምህርት ክፍል ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት፡፡

15. **ስለ ጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና**

1) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6(1) ስር የተደነገጉትን የሚያሟላ ማንኛዉም በጥብቅና አገልግሎት መሰማራት የሚፈልግ ሰዉ የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና መዉሰድ ይኖርበታል፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም በህግ የመጀመርያ ዲግሪ ኖሮት በኢትዮጵያ በሚገኙ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ በህግ መምህርነት ቢያንስ ለወንድ አምስት ዓመት ለሴት አራት ዓመት፤ በማስተርስ ድግሪ ለወንድ አራት ለሴት ሶስት ዓመት፣ በዶክትሬት ድግሪ ሁለት ዓመት ያገለገለ/ች፤

3) በዳኝነት፣ በዐቃቤ ሕግነት፣ በመንግስት መሥሪያ ቤት ወይም በመንግስት የልማት ድርጅት ውስጥ በህግ አማካሪነት ወይም በህግ ባለሙያነት ወይም በነገረ ፈጅነት ቢያንስ ወንድ ለአራት ዓመት ሴት ለሶስት ዓመት ያገለገለ/ች፤

4) በረዳት ዳኝነት፣ በጠበቃ ወይም ጥብቅና ድርጅት የህግ ጉዳይ ፀሐፊነት ወይም የጠበቃ ረዳትነት እንዲሁም በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት፣ በሀይማኖት ተቋማት፣ በአለም አቀፍ ድርጅቶች፣ በንግድ ድርጅቶችና ሌሎች ተቋማት በህግ አማካሪነት ወይም በህግ ባለሙያነት ወይም በነገ ረፈጅነት ቢያንስ ለወንድ ስድስት ዓመት፤ ለሴት አራት ዓመት ያገለገለ/ች ኢትዮጵያዊ/ዊት ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ/ዊት ሥራውን በለቀቀ/ች በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የጥብቅና ፍቃድ ማመልከቻ ያቀረበ/ች እንደሆነ የጥብቅና ፍቃድ ያለፈተና ሊሰጠው/ጣት ይችላል፤

5) ፍትህ ቢሮ የጥብቅና ፈቃድ ገምጋሚ ኮሚቴ ፈቃድ እንዲሰጠዉ ለወሰነለት ባለሙያ የጥብቅና ፈቃድ ይሰጣል፤

16. **የጥብቅና ፈቃድ ደረጃ ስለማሻሻል**

1. የወረዳ ፍርድ ቤት ፈቃድ ያለው ጠበቃ የስራ ልምዱ ወይም የትምህርት ደረጃው ፈቃድ የሚያሰጠው ከሆነ ደረጃው እንዲሻሻልለት ለቢሮው ማመልከት ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገው ቢኖርም የወረዳ ፍርድ ቤት ጥብቅና ፈቃድ ያለው ጠበቃ፤ የመጀመሪያ ዲግሪ ኖሮት በጥብቅና ፈቃዱ ለወንድ አራት ዓመት ለሴት ሶስት ዓመት እንዲሁም፤

3. በህግ ዲፕሎማ ኖሮት በጥብቅና ፈቃዱ ለወንድ ስድስት ለሴት አራት ዓመት ካገለገለ/ች የጥብቅና አገልግሎት ሥራውን/ዋን ሳይተው/ትተዉ የክልሉ ማናቸውም ፍርድ ቤት የጥብቅና ፍቃድ ያለፈተና ሊሰጠው/ጣት ይችላል።

**ንዑስ ክፍል ሁለት**

**ምዝገባ እና እድሳት**

17. **ምዝገባ**

1. ፍትህ ቢሮ የጥብቅና ፍቃድ የተሰጣቸዉን ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች ሙሉ መረጃ መመዝገብ አለበት፤
2. በምዝገባ ስርዓቱ ውስጥ የሚካተቱ ዝርዝር ነጥቦች ፍትህ ቢሮ በሚያወጣዉ መመሪያ ይወሰናል፤
3. ፍትህ ቢሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት አዲስ የመዘገባቸዉን ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች ስም ዝርዝር በየሶስት ወሩ ለማህበሩ ማሳወቅ ይኖርበታል፤
4. ፍትህ ቢሮ የጥብቅና ፍቃድ የተሰጣቸዉን ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች መረጃ ለማህበረሰቡ ተደራሽ እንዲሆን በተለያየ መንገድ ይፋ ያደርጋል።

18. **ከጠበቃ ወይም ጥብቅና ድርጅት ጋር ስለሚሰሩ ሰዎች**

1. ማንኛዉም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የህግ ጉዳይ ጸሀፊ፤ የጠበቃ ረዳት ወይም ሌሎች ለስራዉ የሚያስፈልጉ ሰራተኞችን መቅጠር የሚችል ሲሆን የጥብቅና ድርጅት ከነዚህ ከተጠቀሱት ሰራተኞች በተጨማሪ ጠበቃ ሊቀጥር ይችላል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ቅጥር የፈጸመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ቅጥሩ በተፈጸመ በሁለት ወራት ጊዜ ዉስጥ ስላስቀጠረው ሰው ሙሉ መረጃ ለፍትህ ቢሮ ማሳወቅ እና ማስመዝገብ አለበት፤
3. ማንኛዉም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የሚከተሉትን በህግ ጉዳይ ጸሀፊነት ወይም በጠበቃ ረዳትነት መቅጠር አይችልም፡-

ሀ. የጥብቅና ፍቃዱ የታገደን ወይም የተሰረዘን ሰው፣

ለ. ስሙ ከጠበቆች መዝገብ የተፋቀን ሰው፣

ሐ. ከመስሪያ ቤቱ በዲሲፕሊን ጥፋት የተባረረን ሰው፣

መ. ከስነ-ምግባር ጋር በተያያዘ ወንጀል ተከሶ የተቀጣ እና ያልተሰየመን ሰው፣

ሠ. ቋሚ ስራ ያለዉን ሰው፣

ረ. የሕግ ትምህርት ወይም በህግ ሙያ የስራ ልምድ የሌለዉን ሰው።

19. **ስለፍቃድ እድሳት**

ሀ. የጥብቅና ፍቃድ በየዓመቱ ፍቃዱ ጸንቶ ከሚቆይበት የመጨረሻ ቀን ጀምሮ በአንድ

ወር ጊዜ ውስጥ መታደስ አለበት፤

ለ. ማንኛዉም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ በተጠቀሰዉ ጊዜ ውስጥ ፍቃዱን ሳያሳድስ ከቀረ በሚቀጥለው አንድ ወር ጊዜ ዉስጥ ፍትህ ቢሮ በሚያወጣዉ መመሪያ መሰረት የሚጣልበትን የገንዘብ ቅጣት ከፍሎ ፍቃዱ ይታደስለታል፤

ሐ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጠበቃዉ ወይም የጥብቅና ድርጅቱ ፍቃዱን ያላሳደሰዉ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን የሚያሳይ አሳማኝ ማስረጃ ካቀረበ ፍትህ ቢሮ በሚያወጣዉ መመሪያ መሰረት የሚጣልበትን የገንዘብ ቅጣት ከፍሎ በቀጣዩ አንድ ወር ጊዜ ውስጥ የጥብቅና ፍቃዱ ሊታደስለት ይችላል፤

መ. ማንኛዉም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት በዚህ አንቀጽ መሰረት ፍቃዱን ያላሳደሰ እንደሆነ የዲሲፒሊን ክስ ይቀርብበታል፡፡

20. **ፍቃድ ለማሳደስ የሚቀርቡ ማስረጃዎች**

ማኛዉም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የጥብቅ ፍቃድን ለማሳደስ የሚከተሉትን ማስረጃዎች ማቅረብ ይኖርበታል፡-

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 30(4) መሰረት አስገዳጅ የህግ ስልጠና ከተራዘመለት ጠበቃ በስተቀር ጠበቃዉ በዚህ አዋጅ የተቀመጠዉን የስልጠና ግዴታ ማጠናቀቁን የሚገልጽ ማስረጃ፤
2. ላገኘው ገቢ ግብር ስለመክፈሉ ከግብር አስገቢው አካል የሚሰጥ ማስረጃ ወይም ታክስ ክሊራንስ የማቅረብ፤
3. ለጠበቆች ማህበር መክፈል የሚጠበቅበትን የአባልነት መዋጮ መክፈሉን የሚያረጋግጥ ከማህበሩ የሚሰጥ ማስረጃ፤
4. እድሜዉ ከ65 አመት በላይ የሆነ ጠበቃ ህጋዊ ከሆነ የጤና ተቋም የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የጤና ሁኔታ ላይ ያለ ስለመሆኑ የሚገልጽ ማስረጃ፤ እና
5. በዓመት ዉስጥ መስጠት የሚጠበቅበትን ነጻ የጥብቅና አገልግሎት ስለመስጠቱ የሚያረጋግጥ ማስረጃ፡፡

21. **ፍቃድን ስለመመለስ**

ማንኛውም ጠበቃ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙት የጥብቅና ፈቃዱን ለፍትህ ቢሮ መመለስ አለበት፡-

1. ከሙያው ውጭ በሆነ ሥራ በቋሚነት የተሰማራ እንደሆነ፣
2. የጥብቅና አገልግሎት ለመስጠት ያልቻለ እንደሆነ፣
3. የጥብቅና አገልግሎት ለማቆም ከወሰነ።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ጠበቃዉ ፍቃድ ለመመለስ ሲያመለክት ፍትህ ቢሮ የጥብቅና ፍቃድ ደብተሩን ወዲያዉኑ መረከብ አለበት፣ ሆኖም የጥብቅና አገልግሎቱን ማቋረጡን የሚገልጽ ማስረጃ ለጠበቃዉ የሚሰጠዉ ጠበቃዉ ከሚመለከተዉ አካል የግብር ክሊራንስ ይዞ ሲቀርብ ይሆናል፤
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ፍቃዱን የመለሰ ጠበቃ ወደ ጥብቅና ስራው መመለስ ከፈለገ ፍቃዱን መልሶ ሊወስድ ይችላል፣ ሆኖም ጠበቃው ከጥብቅና አገልግሎቱ ከሁለት ዓመት በላይ ተለይቶ የቆየው ከህግ ሙያ ውጪ በሆነ ስራ ላይ ተሰማርቶ ከሆነ ፍቃዱ የሚመለስለት ለደረጃዉ የሚሰጠውን የጥብቅና መግቢያ ፈተና ወስዶ ካለፈ ብቻ ነው፤

## ክፍል ሶስት

## የጠበቆች የሙያ ግዴታ

## ንዑስ ክፍል አንድ

## ጠቅላላ የጠበቆች ግዴታ

### 22. ከጥብቅና ፍቃድ ጋር የተያያዘ ግዴታ

ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት፡-

1. በደንበኛ፣ በፍርድ ቤት ወይም በማንኛውም አግባብ ባለው አካል የጥብቅና ፍቃድን እንዲያሳይ ሲጠየቅ የማሳየት ግዴታ አለበት፤
2. የጥብቅና ፍቃዱን በማንኛውም ሁኔታ ለሌላ ሰው መጠቀሚያ ወይም መገልገያ አሳልፎ መስጠት የለበትም።

### 23. ስለጥብቅና አገልግሎት ውል እና ተያያዥ ግዴታዎች

1. ማንኛዉም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት በአጭር ጊዜ ዉስጥ ከሚሰጠው የህግ ምክር አገልግሎት ውጭ ከደንበኛው ጋር የሚያደርገውን የጥብቅና አገልግሎት ውል በፅሑፍ ማድረግ አለበት፤
2. የጥብቅና አገልግሎት ውል ማካተት ስለሚገባቸው ነገሮች ማህበሩ በመመሪያ ይወስናል።

3. የጥብቅና አገልግሎት ዉሉ ደንበኛው ለጠበቃው የሚከፍለውን አጠቃላይ የገንዘብ ክፍያ፣ የአከፋፈሉን ስልት እና ጊዜ፣ ጠበቃዉ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠዉን የጥብቅና አገልግሎት የሚያካትት መሆን አለበት፤

4. ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት፡-

ሀ. ለጥብቅና አገልግሎት መስጫ የሚሆን ቢሮ የማሟላት፣

ለ. የጥብቅና ስራን በአገናኝ አማካኝነት ያለመስራት፣ እና

ሐ. የጥብቅና ውልን ያለበቂና ህጋዊ ምክንያት ያለማቋረጥ እና

መ. በጥብቅና ውሉ ከተገለፀው የክፍያ መጠን በላይ ተጨማሪ ክፍያ ከደንበኛ ያለመጠየቅ ግዴታ አለበት፤

5. ሆኖም የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ፈቃድ ሰጪው አካል ቢሮ ማሟላትን እንደመስፈርት ሊጠይቅ አይችልም፡፡

24. **ስለታማኝነትና ለፍትህ አጋር መሆን፤**

1. ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የጥብቅና አገልግሎት ስራውን በታማኝነት የመስራትና ለፍትህ አጋር የመሆን ግዴታ አለበት፤

2. ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት፤

ሀ. ያለበቂ ምክንያት ጉዳይን ያለማጓተት፣

ለ. ምስክሮችን በሐሰት ያለማደራጀት፣

ሐ. ሀሰተኛ ማስረጃ ያለማቅረብ ወይም ያለማስቀረብ፣ ተዘጋጅቶ የመቅረብና ተገቢውን ክርክር የማድረግ፤ የህግ መሰረት የሌለውንና የማያዋጣ ጉዳይን ያለመያዝ፤

ሠ. የደንበኛውን ወይም ባለጉዳዩን ሚስጢር ያለማውጣት እና ሌሎች መሰል የሥነ-ምግባር ግዴታ አለበት፤

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የሕግ ስልጠና የመውሰድ ግዴታ

25. **ዓላማ**

የሕግ ስልጠና ዓላማ የክልሉ የጥብቅና ፈቃድ የተሰጣቸው ጠበቆች የሙያ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት የሚያስችል ወቅታዊ ዕውቀትና ክህሎት በቀጣይነት እንዲኖራቸው ማስቻል ነው፡፡

26. **ስለ የሕግ ስልጠና**

1. ማንኛውም  የክልሉ የጥብቅና ፈቃድ የተሰጠው  ጠበቃ በዓመት ዉስጥ በድምሩ ከ24 እስከ 30  ሰአት የሚደርስ  የሕግ ስልጠና የመውሰድ ግዴታ አለበት፤
2. የህግ ስልጠናው በተከታታይ ወይም በዚያው ዓመት ውስጥ በተለያየ ጊዜ ሊሰጥ ይችላል፤
3. በሕግ ስልጠና የሚሸፈኑ የስልጠና ዘርፎችን፣ የስልጠና ጊዜውን  ርዝመት፤ አጠቃላይ የስልጠና አሰጣጥ መርሃ-ግብር፤ የስልጠና ክፍያ እና ሌሎች ከስልጠና ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በተመለከተ ማህበሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወስናል፡፡

27. ***ዕውቅና ስለተሰጣቸው ተቋማት***

1. የህግ ስልጠና የሚሰጠው ማህበሩ እውቅና በሚሰጠው ተቋም  ይሆናል፤
2. የጥብቅና ድርጅቶች በስራቸው ያሉ ጠበቆችን ስልጠና እንዲሰጡ በማህበሩ እውቅና ሊሰጣቸው ይችላል፣
3. ማህበሩ ለጥብቅና ድርጅት ወይም ለተቋም ዕዉቅና ከመስጠቱ በፊት የሚሰጡ የሥልጠና ዓይነቶችን ቀድሞ ማፅደቅ ይኖርበታል፤ ሆኖም በቅድሚያ የጸደቁት የሥልጠና ዓይነቶች በማህበሩ ወደፊት ሊሻሻሉ፣ ሊታገዱ፣ ወይም ሊሠረዙ ይችላሉ፤
4. የተከታታይ የሕግ ስልጠና ሰጪዎች ዕውቅና የሚያገኙበት ሥነ ሥርዓት እና መሥፈርቶች በተመለከተ ማህበሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

28. ***ሪፖርት የማድረግ ኃላፊነት***

1. የስልጠና ተቋሙ በስልጠና ላይ ያሉትን ሰልጣኞች ስልጠና ከጀመሩበት እንዲሁም ስልጠና ያጠናቀቁ ሰልጣኞችን ስልጠናውን ካጠናቀቁበት ጊዜ ጀምሮ ባለው አንድ ወር ጊዜ ዉስጥ ለማህበሩ ማሳወቅ አለበት፤
2. ማንኛዉም ጠበቃ ማህበሩ ባሳወቀው የስልጠና ጊዜ ለመሰልጠን የማያስችል በቂ ምክንያት ካለው ምክንያቱን ለማህበሩ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

29. **የሕግ ስልጠና አለመከታተል**

1. ማንኛዉም ጠበቃ በዚህ ንዑስ ክፍል የተቀመጡትን የሕግ ስልጠና ግዴታዎች ሳያሟላ የቀረ እንደሆነ ማህበሩ ይህንኑ ለፍትህ ቢሮው በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፤
2. ፍትሕ ቢሮው  ከተከታታይ የስልጠና ግዴታ ጋር ተያይዞ ያለበቂ ምክንያት የስልጠና ግዴታውን ለመውሰድ ፈቃደኛ  ባልሆነ ጠበቃ ላይ የድሲፕሊን ክስ ሊመሰርትበት ይችላል፡፡

30. **የህግ ስልጠና ግዴታን ስለማራዘም**

1. ማንኛውም ጠበቃ በአሳማኝ ምክንያት ማህበሩ በሚያወጣው የስልጠና ጊዜ ውስጥ የስልጠና ግዴታውን መውሰድ ካልቻለ ጠበቃው ስልጠናውን ማህበሩ ባወጣው ጊዜ ውስጥ መውሰድ ስላለመቻሉና የስልጠና ጊዜው እንዲራዘምለት ማህበሩ ከያዘው የስልጠና ጊዜ ከአንድ ወር በፊት ቀድሞ ለማህበሩ በማመልከቻ ማሳወቅ አለበት፤
2. ጠበቃዉ የስልጠና ጊዜዉ እንዲራዘምለት የሚያቀርበዉ ማመልከቻ ስልጠናዉን መዉሰድ እንዳይችል ያደረገውን ምክንያት፣ ስልጠናዉን ለመዉሰድ ያደረገውን ጥረት፤ እና በቀጣይ መቼና በምን አግባብ እንደሚወስድ ያለውን ዕቅድ የሚገልጽ መሆን አለበት፤
3. ማህበሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የቀረበለት ማመልከቻ አሳማኝ ሆኖ ካገኘው የስልጠና ጊዜውን በዚያው ዓመት ውስጥ ጠበቃው በጠየቀው ጊዜ ወይም እራሱ በመሰለው ጊዜ ሊቀይርለት ይችላል፤ ማህበሩ ጥያቄዉን ከተቀበለዉ የቅያሪውን ሁኔታ ወይም ጥያቄውን ካልተቀበለው ያልተቀበለው መሆኑን በ15 ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ለጠበቃው ማሳወቅ አለበት፤
4. ጠበቃው በዓመት መውሰድ የሚጠበቅበትን የህግ ስልጠና ግዴታ በዚያው ዓመት አጠቃሎ መውሰድ ካልቻለ እና ስልጠናዉን ያልወሰደዉ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ስለመሆኑ ማስረጃ ካቀረበና ማህበሩ ካመነበት ጠበቃው ያልወሰደውን የስልጠና ጊዜ ወደ ቀጣይ ዓመት በማሸጋገር በቀጣይ ዓመት መውሰድ ከሚጠበቅበት የስልጠና ግዴታ ጋር ደርቦ እንዲወስድ ሊፈቅድለት ይችላል፡፡

**ንዑስ ክፍል ሶስት**

**ስለ ነጻ የጥብቅና አገልግሎት ግዴታ**

**31. ነጻ የጥብቅና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ**

ሀ. ማንኛዉም በጥብቅና ድርጅት ዉስጥ ሽሪክ ሆኖ ወይም ተቀጥሮ የሚሰራ ጠበቃ፤ ወይም በግሉ የሚሰራ ጠበቃ እንደጉዳዩ ክብደት እና ቅለት እየታየ በዓመት ከሶስት ጉዳይ ያልበለጠ ነጻ የጥብቅና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት፤ አገልግሎቱ የሚሰጠዉም፡-

1. የመክፈል አቅም ለሌላቸዉ ሰዎች፣
2. ከሚኖሩበት ቦታ ከህግ አግባብ ውጭ ለተፈናቀሉ ሰዎች፤
3. በኤች አይ ቪ ቫይረስ ምክንያት ወላጆቻቸውን አጥተው ለአካለ መጠን ላልደረሱ ልጆች ወይም በዚሁ በሽታ ምክንያት ልጆቻቸውን አጥተው በእድሜ ለገፉ ወላጆች፤

4. በምርምር፣ በስፖርት፣ በማስተማር፣ በፈጠራ ስራ፣ በጦርነት ጀብድ በመስራት እና በሌሎች መስኮች ተሳትፈው ሃገርን ያስጠሩ ሰዎች መሆናቸው በክልሉ መንግስት እውቅና ለተሰጣቸው፤
5. ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች፤ ለሲቪክ ማህበራት፤ እና ለማህበረሰብ ተቋማት፣
6. ፍርድ ቤት ነፃ የጥብቅና አገልግሎት እንዲያገኙ ለሚጠይቅላቸዉ ሰዎች፣
7. ሕግን፤ የህግ ሙያን እና የፍትህ ስርአቱን ለማሻሻል ለሚሰሩ ኮሚቴዎች እና ድርጅቶች ነዉ፡፡

ለ. ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ለሕዝብ ነጻ የጥብቅና አገልግሎት ግዴታውን መወጣቱን የሚገልጽ ማህደር መያዝ የሚኖርበት ሲሆን፤ ማህደሩም እያንዳንዱ አገልግሎት የተሰጠበትን ቀን፣ የአገልግሎት አይነቱን እና አገልግሎቱ የወሰደውን ጊዜ የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

32. **ነፃ የጥብቅና አገልግሎት ስለመምራት**

1. ፍትህ ቢሮው እያንዳንዱ ጠበቃ በዓመት መስጠት ከሚጠበቅበት የነፃ የጥብቅና አገልግሎት መጠን ሳያልፍ በነፃ የጥብቅና አገልግሎት ሊስተናገዱ የሚገባቸውን ጉዳዮች እያጣራ ለጠበቆች ይመራል፤
2. እያንዳንዱ ጠበቃ በዓመት መስጠት ከሚጠበቅበት የነፃ የጥብቅና አገልግሎት ግዴታ ሳያልፍ በፍትሕ ቢሮው የሚመራለትን የነፃ ጥብቅና አገልግሎት ተቀብሎ የመስራት ግዴታ አለበት፤
3. ማህበሩ ፍትሕ ቢሮው የነፃ የጥብቅና አገልግሎት እንዲሰጥ የመራለትን ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት በዚህ አዋጅ እና በጠበቆች ስነ-ምግባር ደንብ መሰረት መፈጸሙን መቆጣጠር እና መከታተል አለበት፤
4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም በጠበቃው በኩል ነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎት መሰጠት ያለበት ሰው አግኝቶ አገልግሎቱን በነፃ የሰጠ በሆነ ጊዜ ፍትሕ ቢሮው የአገልግሎቱን ትክክለኛነትና አውነተኛነት አረጋግጦ እውቅና ሊሰጠው ይችላል፣

## ንዑስ ክፍል አራት

## መድን እና የደንበኞች ንብረት

33. *የሙያ ኃላፊነት መድን የመያዝ ግዴታ*

ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ሥራውን በአግባቡ ሳይወጣ በመቅረቱ ምክንያት በደንበኛው ላይ ሊደርስ ለሚችል ጉዳት ካሳ የሚሆን የሙያ ኃላፊነት መድን መያዝ አለበት፡፡

34. **የመድን ሰጪው ግዴታዎች**

1. ለጠበቃ ወይም ለጥብቅና ድርጅት የሙያ ኃላፊነት መድን የሰጠ መድን ሰጪ የመድን ውሉ ሲቋረጥ ወይም ግዴታው እንዳይፈፀም ሊያደርግ የሚችል ሁኔታ ሲፈጠር ሁኔታውን ወዲያውኑ ለፍትህ ቢሮ ማሳወቅ አለበት፣
2. መድን ሰጪው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተቀመጠውን ግዴታውን ባለመወጣቱ ለሚደርሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት፡፡

35. **የደንበኛን ንብረት ስለማስተዳደር**

ማንኛዉም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት፡-

1. ከሙያ ሥራው ጋር በተገናኘ በይዞታው ወይም በአስተዳደሩ ሥር የሚገኝን የደንበኛው ወይም የሦስተኛ ወገንን ንብረት አስተዳደርን ጥበቃ ከራሱ ንብረት ፍጹም በማይገናኝበት ሁኔታ ለይቶ ማስተዳደር አለበት፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሱትን የደንበኛው ወይም የሶስተኛ ወገን ንብረቶች የሚመለከቱ ማናቸውንም ሰነዶች ጉዳዩ ካለቀበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አምስት ዓመት ድረስ የመያዝ ግዴታ አለበት፡፡

36. **የደንበኛ የአደራ ሒሳብ**

1. በጠበቃው ወይም በጥብቅና ድርጅቱ እጅ የሚገኝ የደንበኛ ገንዘብ ከጠበቃው ወይም ከጥብቅና ድርጅቱ በተለየ ሒሣብ ዉስጥ መቀመጥ አለበት፤
2. ቦርዱ ጠበቆች ወይም የጥብቅና ድርጅቶች የደንበኞች አደራ ሒሳብ ለመያዝ ማሟላት የሚገባቸውን መስፈርቶች በመመሪያ ሊወሰን ይችላል፤
3. የደንበኛው የአደራ ሂሳብ በጠበቃው ወይም በጥብቅና ድርጅቱ ማንቀሳቀስ የሚቻለው ክፍያ ሊፈፀምባቸው የሚገቡ ስራዎች መከናወናቸውን እና በደንበኛው ስም መደረግ ያለባቸው ወጪዎች በበቂ ማስረጃ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፤
4. ጠበቃው ወይም የጥብቅና ድርጅቱ የደንበኛዉ ወይም የሦስተኛ ወገን ጥቅም ያለበት ገንዘብ ወይም ሌላ ንበረት ሲቀበል ለደንበኛው ወይም ለሦስተኛ ወገን ወዲያው ማሳወቅ አለበት፤
5. በዚህ አዋጅ ከተመለከተው ወይም በህግ ወይም ከደንበኛው ጋር በተደረገ ስምምነት ካልተፈቀደ በስተቀር አንድ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ለክፍያ ያልዋለ በአደራ ሂሳብ ውስጥ የተቀመጠን ገንዘብ ደንበኛው ወይም መብት ያለው ሶስተኛ ወገን ሲጠይቅ ወይም ጉዳዩ ሲጠናቀቅ ወዲያውኑ ከበቂና የተሟላ ሪፖርት ጋር ማስረከብ አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## ስለጥብቅና ድርጅት

37. **የጥብቅና ድርጅት ስለማቋቋም**

በዚህ አዋጅ መሰረት የፀና የጥብቅና ፈቃድ ያላቸው ቢያንስ ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ ጠበቆች አንድ ላይ በመሆን የጥብቅና ድርጅት ማቋቋም ይችላሉ፡፡

38. **የአገልግሎት ወሰን**

1. የጥብቅና ድርጅት ዋነኛ ተግባር የጥብቅና አገልግሎት መስጠት ነው፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተደነገገው እደተጠበቀ ሆኖ የጥብቅና ድርጅት ከጥብቅና አገልግሎት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሌሎች አገልግሎቶች ሊሰጥ ይችላል፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም ፍትህ ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

39. **የጥብቅና ድርጅት አደረጃጀት እና ኃላፊነት**

1. የጥብቅና ድርጅት ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር አደረጃጀት ይኖረዋል፤
2. የጥብቅና ድርጅት ውል የመዋዋል፣የንብረት ባለቤት የመሆን፣ በስሙ የመክሰስና የመከሰስ እና የህግ ሰዉነት ያለዉ ድርጅት የሚኖረዉ ሌሎች መብት እና ግዴታዎች ይኖሩታል፡፡
3. የጥብቅና ድርጅት ሽሪኮች ለሶስተኛ ወገን የሚኖርባቸው ኃፊነት በጥብቅና ድርጅቱ ውስጥ ባላቸው የመዋጮ ድርሻ ልክ የተወሰነ ይሆናል፤
4. የጥብቅና ድርጅት አባላትን የሚመለከት ለውጥ ቢመጣም የጥብቅና ድርጅት ህልውና ይቀጥላል፤
5. የጥብቅና ድርጅት የጥብቅና አገልግሎት መስጠቱ በንግድ እና ኢንቨስትመንት ሕጎች መሠረት አገልግሎቱን የንግድ ወይም የኢንቨስትመንት ሥራ አያሰኘውም፡፡

40. **ስለ ጥብቅና ድርጅት ስያሜ**

1. የጥብቅና ድርጅት አባላት ማንኛውንም ስያሜ የጥብቅና አገልግሎት ድርጅቱ መጠሪያ እንዲሆን መምረጥ እና መወሰን ይችላሉ፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም ለጥብቅና ድርጅቱ መጠሪያነት የተመረጠው ስም በሚከተሉት ምክንያቶች በፍትሕ ቢሮው ተቀባይነት ላይኖረዉ ይችላል፡-

    ሀ. ከሌላ የጸና የጥብቅና ድርጅት ስም ጋር ተመሳሳይ ከሆነ፣

    ለ. ደንበኞች ድርጅቱን ከሌላ የጥብቅና ድርጅት በቀላ መለየት እንዳይችሉ

በሚያስችል   መልኩ ሊያሳስት ወይም ሊያደናግር የሚችል ከሆነ እና

ሐ. ለሕግ ወይም ለሕዝብ ሞራል ተቃራኒ ከሆነ፡፡

3. የጥብቅና ድርጅት ስም የጥብቅና ድርጅት መሆኑን የሚያመለክትና ከስሙ በስተመጨረሻ "ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር" ወይም ("ኃ.የተ.የሽ.ማ") የሚል ሐረግ ያለው መሆን አለበት፤
4. በጥብቅና ድርጅቱ ስም የሚወጡ ሰነዶች በሙሉ በግልጽ ስሙን እና "ኃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማኅበር" የሚለውን ሐረግ መያዝ አለባቸው፡፡

41. ***የመቋቋሚያ መሥፈርቶችና ሥነ ሥርዓቶች***

1. የጥብቅና ድርጅት በፍትሕ ቢሮው በመመዝገብ ይቋቋማል፤
2. የጥብቅና ድርጅት ለማቋቋም የሚከተሉት ሰነዶች ከማመልከቻ ጋር ተያይዘው ለፍትሕ ቢሮው መቅረብ አለባቸው፡-
3. የሽሪኮቹን ሙሉ ስምና ፊርማ የያዘ  ማመልከቻ፣

   ሀ. የድርጅቱን መመስረቻ ጽሁፍ፤

   ለ. የሽሪኮቹ የጥብቅና ፈቃድ ቅጂ፣ እና

   ሐ. ሽሪኮች ድርጅቱን ለመመስረት የተስማሙበትን የሽርክና ስምምነት፤ የጥብቅና ድርጅቱን ስም፤ የሽርክና ማህበሩን የቆይታ ዘመን፤ የድርጅቱ ዓላማ በአጭሩ የተገለጸበት እና በምስረታ ሂደት ድርጅቱን የሚወክለዉ ሽሪክ የተሰየመበት ቃለ-ጉባኤ፤

4. የጥብቅና ድርጅት መመስረቻ ጽሁፍ በንግድ ህጉ ሀላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማህበር መመስረቻ ጽሁፍ ሊያካትታቸዉ የሚገቡ ዝርዝሮችን ማካተት  ይኖርበታል፤
5. ፍትሕ ቢሮው የቀረቡለት ሰነዶች ከዚህ አዋጅ አግባብነት ካላቸው ሌሎች ሕግጋት ጋር የተጣጣሙ መሆናቸዉን ካረጋገጠ ማመልከቻውን በተቀበለ በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ የጥብቅና ድርጅቱን ይመዘግባል፤ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤
6. ፍትህ ቢሮ የቀረቡለት ሰነዶች ከዚህ አዋጅና አግባብነት ካላቸው ሌሎች ሕጎች ጋር የሚጣረሱ ናቸው ብሎ ካመነ ማመልከቻውን በተቀበለ በ20 የሥራ ቀናት ውስጥ ውድቅ ማድረግና ማመልከቻው ውድቅ እንዲሆን መነሻ የሆነውን ምክንያት በመግለጽ ለአመልካቹ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፤

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) መሠረት ያቀረበው ማመልከቻ ውድቅ የተደረገበት አካል ቅሬታዉን ማመልከቻዉ ዉድቅ መደረጉን ባወቀ በ15 የስራ ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል፤
8. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (7) መሰረት ቦርዱ በሚሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን ውሳኔ በተሰጠ በ15 የስራ ቀናት ውስጥ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፤የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍሬ ነገር ጉዳይ የሚሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

42. **የመዋጮ ዓይነትና መጠን**

ሀ. የጥብቅና ድርጅት ሽሪኮች ዋነኛው መዋጮ ክህሎት መሆን አለበት፤

ለ. ሽሪኮች መዋጮዎችን በገንዘብ ወይም በዓይነት ማዋጣት ይችላሉ፤

ሐ. የጥብቅና ድርጅት ሽሪኮች የመዋጮ መጠን የድርጅቱን ዓላማ ለማሳካት የሚበቃ መሆን ያለበት ሆኖ በገንዘብ የሚደረገዉ መዋጮ ከሀምሳ ሺህ ብር ማነስ የለበትም፤

መ. ገንዘብ ባልሆነ ማናቸውም መንገድ በጥብቅና ድርጅት ሽሪክ የሚደረግ መዋጮ ዋጋ በሁሉም ሽሪኮች ስምምነት እና አግባብነት ባላቸው ሕግጋትና ደንቦች ይወሰናል፡፡

43. **የሽሪኮች መብትና ግዴታ**

1. የጥብቅና ድርጅት ሽሪክ የሚከተሉት መብቶች አሉት፡-

ሀ.ጥብቅና ድርጅቱ ስብሰባዎች የመካፈል እና ድምጽ የመስጠት፣

ለ.ድርሻው መጠን ከጥብቅና ድርጅቱ ትርፍ ወይም የጥብቅና ድርጅቱ ሲከስም ከተጣራው የማኅበሩ ሐብት ከሚተርፈው ሐብት የመካፈል፤

ሐ. ጥብቅና ድርጅቱን አጠቃላይ አሰራር የመከታተል፣ የማወቅ፤

መ.ሽርክና ስምምነት፣ በዚህ አዋጅና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች የተመለከቱ፣ ወይም ከሽርክና ማኅበሩ ተፈጥሮ የሚመነጩ ሌሎች መብቶችና ጥቅሞችን የመጠቀም፡፡

2. የጥብቅና ድርጅት ሽሪክ የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት፡-

ሀ.ጥብቅና ድርጅቱ መክፈል የሚጠበቅበትን መዋጮ በወቅቱ መክፈል፣

ለ. ማናቸውም ጊዜ የጥብቅና አገልግሎት ድርጅቱን ዓላማ ለማሳካት በትጋት የመሥራት፣

ሐ. ራሱ ጥቅም የሚያስገኝ ቢሆንም ባይሆንም የጥብቅና ድርጅቱን ጥቅም ከሚጻረሩ ድርጊቶች ወይም ኃላፊነትን ከሚያጓድሉ ተግባራት መታቀብ፣ እና

መ. ሽርክና ስምምነት፤ በዚህ አዋጅ፣ አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች፣ በሽርክና ስምምነት የተመለከቱ ወይም ከሽርክና ማኅበሩ ተፈጥሮ የሚመነጩ ሌሎች ግዴታዎችን የመወጣት፡፡

44. **ስለትርፍ እና ኪሣራ ክፍፍል**

በጥብቅና ድርጅቱ የሽርክና ስምምነት በተለየ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር የማኅበሩ ሽሪኮች የድርጅቱን ትርፍ እና ኪሳራ ወይም የጥብቅና ድርጅቱ ሲከስርም ከተጣራው የማኅበሩ ሐብት የሚተርፈውን ሐብት በድርጅቱ ዉስጥ ባላቸዉ ድርሻ መጠን የመካፈል መብት አላቸው፡፡

45. **የሽሪኮች ለውጥ፤**

ሀ.አግባብነት ባለው ሌላ ሕግ የተጣለው ክልከላ እንደተጠበቀ ሆኖ የጥብቅና ድርጅቱን ለሚለቅ ሽሪክ የድርሻው ዋጋ እና የትርፍ ድርሻው ሊከፈለው ይገባል፤

ለ. የጥብቅና ድርጅት ሽሪክ በሚሞትበት ጊዜ ሽሪኩ ሊከፈለዉ የሚገባ ያልተከፈለዉ የትርፍ ድርሻ ለህጋዊ ወራሾቹ ይተላለፋሉ፤

46. **ባለቤትነት**

የጥብቅና ድርጅት ባለቤት መሆን የሚችሉት የፀና የጥብቅና ፍቃድ ያላቸው ጠበቆች ብቻ ናቸዉ፡፡

47. **በጥብቅና ድርጅት ስር በሚሠሩ ጠበቆች ላይ የተጣለ ክልከላ**

1. በጥብቅና ድርጅት ውስጥ ሽሪክ ሆኖ የሚሠራ ማንኛውም ጠበቃ ወይም በጥብቅና ድርጅቱ ውስጥ ተቀጥሮ የሚሰራ ሠራተኛ የሽርክና ወይም የሥራ ቅጥር ዘመኑ ጸንቶ ባለበት ጊዜ መሳተፍ የማይችልባቸዉ ተግባራት፡-

ሀ/ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሌላ የጥብቅና ድርጀት ሽሪክ ወይም ሠራተኛ መሆን፣

ለ/ በሚሠራበት የጥብቅና ድርጅት ውስጥ የተጣለበትን ግዴታ ለመወጣት አስፈላጊ መሆኑ በድርጅቱ ቀደም ብሎ ካልፈቀደ በስተቀር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ሌላ የጥብቅና ድርጀትን መርዳት ወይም መተባበር፣

ሐ/ የግል የጥብቅና አገልግሎት መስጠት፤

መ/ የጥብቅና ድርጅቱ ሳያውቅና ሳይፈቅድ በጥብቅና ድርጅቱ በኩል ሲስተናገድ ከነበረ ደንበኛ በራሱ ስም የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ መቀበልና ለግል ጥቅም ማዋል፤

ሠ/ ማንኛውንም ከጥብቅና ድርጅቱ አላማና ተግባር ጋር የሚጣረስና የጥቅም ግጭት ሊፈጥር የሚችል ስራ በግሉም ሆነ ተቀጥሮ መስራት፤

ረ/ የጥብቅና ድርጅቱን ሥራ በሽፋንነት በመጠቀም የግል ጥቅም ለማግኘት በማሰብ በሚፈፅመው ድርጊት በባለጉዳይ ወይም በማንኛውም ሶስተኛ ወገን ላይ ለሚደርስ የፍትሐብሔር ጉዳት በግሉ ኃላፊነት የመውሰድ፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገዉ ቢኖርም ማንኛዉም ጠበቃ በጥብቅና ድርጅት ሽሪክ ወይም ተቀጣሪ ከመሆኑ በፊት የያዘዉ ጉዳይ ደንበኛዉ በተለየ ሁኔታ ካልተስማማ በስተቀር በተያዘበት አግባብ ፍጻሜ ያገኛል፡፡

48. **የጥብቅና ድርጅት አስተዳደር**

1. የጥብቅና ድርጅት በሽሪኮች ውሳኔ በተሾሙ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ቁጥር ባላቸው ሥራ አስኪያጆች ይተዳደራል፤
2. የጥብቅና ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ከድርጅቱ ሽሪኮች መካከል የሚመረጥ መሆን አለበት፤
3. የጥብቅና ድርጅት ስራ አስኪያጅ ድርጅቱን በዋናነት ያስተዳድራል፣ማንኛውንም ህጋዊ የድርጅቱን መብት ለማስጠበቅና የድርጅቱን ግዴታ ለመወጣት የጥብቅና ድርጅቱን ይወክላል፣ የድርጅቱ ተጠሪ ይሆናል፣ ድርጅቱን ወክሎ ይከሳል፣ይከሰሳል፣ ይከራከራል፣ጠበቃ ወይም ሶስተኛ ወገን ይወክላል፤
4. የጥብቅና ድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ስራዉን በሚያከናዉንበት ወቅት የግል ጥቅም ለማግኘት በማሰብ በሚፈፅመው ስህተት ምክንያት በሦስተኛ ወገኖች ላይ ለሚደርስ ጉዳት ስራ አስኪያጁ ኃላፊ ይሆናሉ፤
5. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 47(1)(ረ) እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ከተመለከቱት ውጪ ከውል ወይም በሌላ በማንኛውም ሁኔታ ለሚመጣ የፍትሐብሔር ኃላፊነት ተጠያቂ የሚሆነው የጥብቅና ድርጅቱ ነው፤

49. **የሥራ አስኪያጅ ግዴታዎች**

1. ሥራ አስኪያጁ በሽርክና ስምምነቱ፣ በዚህ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት የተጣሉበትን ግዴታዎች መወጣት አለበት፡

2. የጥብቅና ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ድርጅቱ በውስጠ ደንቦች፣ በሽርክና ስምምነቱ፣ በዚህ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት የተጣሉበትን ግዴታዎች መወጣቱን ማረጋገጥ አለበት፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተጠቀሰው ጠቅላላ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ስራ አስኪያጁ፡-

ሀ. አጠቃላይ የጥብቅና ድርጅቱን የጥብቅና አገልግሎት አሰጣጥ እንቅስቃሴ የመቆጣጠር፣

ለ. ደንበኞች የሚቀርቡ ቅሬታዎችን መቀበል እና መፍታት፤ አግባብ ሆኖ ሲያገኘው ለሚመለከተው አካል የማሳወቅ፣

ሐ. ድርጅቱን የስራ ክንውን ሪፖርት የማዘጋጀትና ለሚመለከተው አካል ሪፖርት የማቅረብ፣

መ. ድርጅቱን ኦዲት የማስደረግና መክፈል የሚጠበቅበትን ታክስ በታክስ ህጉ መሰረት በወቅቱ የማሳወቅና የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡

50. **የጥብቅና ድርጅቱ ውሳኔዎች**

1. የጥብቅና ድርጅቱ በሽርክና ስምምነት ወይም ተፈጻሚነት ባለው ሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተሰወነ በስተቀር ቢያንስ ከግማሽ በላይ ድርሻ ያላቸዉ አባላቱ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፤
2. የጥብቅና ድርጅቱ ሽሪኮች በተለየ ሁኔታ ካልተስማሙ በስተቀር የጥብቅና ድርጅቱ ውሳኔዎች የሚጸድቁት ስብሰባ ላይ ከተገኙት ሽሪኮች ቢያንስ 60% (ስድሳ ከመቶ) ድርሻ ያላቸዉን ሽሪኮች ድምጽ ድጋፍ ሲያገኝ ነው፤
3. የጥብቅና ድርጅቱ ሽሪኮች በተለየ ሁኔታ ካልተስማሙ በስተቀር የማህበሩን መመስረቻ ጽሁፍ ለማሻሻል ስብሰባ ላይ ከተገኙት አባላት የ2/3 (ሁለት ሶስተኛ) ሽሪኮች ይሁንታ ድምጽ ማግኘት ይኖርበታል፤
4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የጥብቅና ድርጅት የስብሰባ ሥነ ሥርዓትና የውስጥ አሰራሩን በተመለከተ ውስጠ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

51. **ግብር**

የማንኛዉም የጥብቅና ድርጅት ወይም ሽሪክ የግብር አከፋፈል አግባብነት ባላቸዉ የሽርክና ማህበርን በሚመለከቱ የግብር ህጎች የሚወሰን ይሆናል፤

52. **ህልዉና እና መፍረስ**

1. የጥብቅና ድርጅት ህልውና በሽሪኮቹ ሞት፣ መልቀቅ፣ ችሎታ ማጣት ወይም ሽሪኮቹን በሚያውክ ማናቸውም ለውጥ አይፈርስም፤

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የጥብቅና ድርጅት ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ሊፈርስ ይችላል፡-

ሀ. የሽርክና ማኅበሩን ለማፍረስ ሽሪኮች ሲስማሙ፣

ለ. የጥብቅና ድርጅቱ መክሰሩ በፍርድ ቤት ሲታወጅ፣

ሐ. የሁሉም ሽሪኮቹ የጥብቅና ፈቃድ ሲሰረዝ፣ ወይም

መ.የፀና የጥብቅና ፈቃድ ያላቸው ሽሪኮች ቁጥር ወደ አንድ ዝቅ ሲልና ቁጥራቸው በጎደለ በስድስት ወራት ውስጥ የጸና የጥብቅና ፍቃድ ያላቸዉ ሽሪኮቹ ቁጥር ቢያንስ ወደ ሁለት ካላደገ፤

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2(መ) ድንጋጌ ቢኖርም የስድስት ወራት የግዜ ገደብ ከማለፉ በፊት በጥብቅና ድርጅቱ የቀረዉ ሽሪክ ለፍትሕ ቢሮው ጥያቄ ሲያቀርብና ፍትሕ ቢሮው ጥያቄዉን አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ የስድስት ወራቱ የግዜ ገደብ በሶስት ወራት እንዲራዘም ሊፈቅድ ይችላል፤

4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 3 በተደነገገዉ መሰረት ካልሆነ በስተቀር የሽሪኮች ቁጥር ወደ አንድ ዝቅ ያለ መሆኑን የሚያዉቅ ሽሪክ የጥብቅና ድርጅቱ በዚህ ሁኔታ ከስድስት ወራት በላይ ስራዉን እንዲቀጥል ካደረገ ለድርጅቱ እዳ እና ግዴታዎች ከጥብቅና ድርጅቱ ጋር በአንድነት እና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ፤

5. የጥብቅና ድርጅት ሲፈርስ ከመዝገብ ይሰረዛል፤

6. ሃላፊነቱ የተወሰነ ማህበርን መፍረስ የሚመለከቱ በንግድ ህጉ ወይም በሌሎች ህጎች የተቀመጡ ድንጋጌዎች የጥብቅና ድርጅት መፍረስን በሚመለከት ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

53. **የጥብቅና ድርጅት እና ሽሪኮች ኃላፊነት፤**

በሽርክና ስምምነቱ ከተፈቀደው ውጭ በያዙት ጉዳይ ላይ ያልተገባ ተግባር ካልፈፀሙ ወይም ሥራቸውን በአግባቡ ባለመወጣታቸው ወይም በማታለል ወይም አውቀው ባደረሱት ጉዳት ካልሆነ በስተቀር ከጥብቅና አገልግሎት መስጠት ጋር በተያያዘ በጠበቆችና ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች አማካኝነት በደንበኞች እና ሌላ ሶስተኛ ወገን ላይ የሚደርስ ጉዳት በጥብቅና ድርጅቱ የደረሰ ጉዳት እንደሆነ ተቆጥሮ ድርጅቱ ሀላፊነት ይወስዳል፤

54. **ገንዘብ ጠያቂዎች**

ሀ. የጥብቅና ድርጅቱ ገንዘብ ጠያቂዎች ከድርጅቱ ማናቸውም ሐብት ላይ ገንዘብ መጠየቅ ይችላሉ፤

ለ. ጥብቅና ድርጅቱ ላይ ገንዘብ የሚጠይቁ ሰዎች ከሸሪኮች የግል ንብረት ላይ ገንዘብ መጠየቅ አይችሉም፡፡

55. **የጥብቅና ድርጅት ግዴታዎች**

በዚህ አዋጅ እና በንግድ ህጉ ስለሃላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማሕበር የተቀመጡት ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው የጥብቅና ድርጅት የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት፡-

1. ከሸሪኮቹ የሙያ ኃላፊነት መድን በተጨማሪ የጸና የሙያ ኃላፊነት መድን መግዛትና ሥራውን በሚያከናውንበት ወቅት ይዞ መገኘት፣
2. ተገቢውን የሒሳብ ሰነድ መያዝ፣
3. የደንበኞቹን ምሥጢር መጠበቅ፣
4. በውጭ ኦዲተር በየዓመቱ ኦዲት መደረግ፣
5. ይህንን አዋጅ፣ አግባብነት ያላቸውን ሌሎች ሕጎችና የሙያ ሥነ ምግባር ደንቦችን ማክበር፣ እና
6. በሽርክና ስምምነቱ ላይ ማሻሻያዎች ሲያደርግ ማሻሻያው በተፈረመ በ30 ቀናት ውስጥ  ለፍትሕ ቢሮው ግልባጩን የማቅረብ፡፡

56. **የሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት**

1. ማንኛዉም የጥብቅና ድርጅት ሸሪክ ከማህበሩ ስለሚወጣበት ሁኔታ እና የወጣ ሸሪክን ድርሻ በተመለከተ ሀላፊነቱ የተወሰነ የሽርክና ማህበርን የተመለከቱ አግባብነት ያላቸዉ የንግድ ህጉ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፤
2. በዚህ አዋጅ ከሚመራዉ የጥብቅና  ድርጅት ተፈጥሮ ጋር የማይቃረኑ እስከሆነ ድረስ የንግድ ህጉ እና አግባብነት ያላቸዉ ሌሎች ህጎች በዚህ አዋጅ መሰረት በሚቋቋም የጥብቅና ድርጅት ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## ክፍል አምስት

## የጥብቅና አገልግሎት አስተዳደር

### ንዑስ ክፍል አንድ

### የጠበቆች ማህበር

57. **መቋቋም**

1. የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ጠበቆች ማኅበር ከዚህ በኋላ “ማህበሩ” እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤
2.  ማኅበሩ ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት አለው፤

3. ማኅበሩ ሁሉንም በፍትሕ ቢሮው የጥብቅና ፍቃድ የተሰጣቸውን ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች በአባልነት ያቀፈ ነው፤

4. ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የጥብቅና ፍቃድ ሲሰጠው ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የማህበሩ አባል ይሆናል፡፡

58. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የማኅበሩ ዋና መሥሪያ ቤት በክልሉ ዋና ከተማ አሶሳ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ቅርንጫፍ ቢሮዎች ሊከፍት ይችላል፡፡

59. **የመጀመሪያ ጠቅላላ ጉባኤ ስለመጥራት**

1. ፍትህ ቢሮው ይህ አዋጅ ከፀናበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ስድስት ወር ባለው ጊዜ ውስጥ የማህበሩን የመጀመሪያ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ይጠራል፤
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የተጠራው ጠቅላላ ጉባኤ የማህበሩን አመራር አካላት ይሰይማል፡፡

60. **ስለ በጀት**

1. የማህበሩ ዋነኛ የገቢ ምንጭ ከአባላቱ የሚሰበሰብ መዋጮ ይሆናል፤
2. ማህበሩ ከሌሎች ህጋዊ ምንጮች የሚያገኛቸዉ ገቢዎች እንደተጠበቁ ሆኖ እራሱን እስኪችል ድረስ ከክልሉ መንግስት የገንዘብ እና ሌሎች ድጋፎች ይደረጉለታል፡፡

61. **የማህበሩ አቋም**

1) ማኅበሩ የሚከተሉት አመራር አካላት ይኖሩታል፡-

   ሀ) ጠቅላላ ጉባኤ፣

   ለ) ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ፣

   ሐ) ፕሬዝዳንት እና ምክትል ፕሬዝዳንት፣ እና

   መ) ዋና ፀሐፊ፣

2) ማህበሩ ሌሎች ሰራተኞች እና እንደ አስፈላጊነቱ ስራዉን ለማከናወን የሚያስችሉ ኮሚቴዎች ወይም በስሩ የሚሰሩ የስራ ክፍሎች ሊኖሩትይችላል፡፡

62. **የማህበሩ ስልጣን እና ተግባራት**

ማህበሩ የሚከተሉት ስልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ተከታታይ የሕግ ስልጠናን በበላይነት ይመራል፤ የተከታታይ የህግ ስልጠናን የሚመለከቱ የአዋጁን ድንጋጌዎች ያስፈጽማል፤
2. የተከታታይ የሕግ ስልጠና ሰጪዎችን እውቅና ይሰጣል፤

3. ይህንን አዋጅ እና  አዋጁን ለማስፈፀም የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን በሚጥሱ የተከታታይ የሕግ ስልጠና ሰጪዎች ላይ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፤
4. ከተከታታይ የሕግ ስልጠና ጋር በተያያዘ የሚፈጸሙ ክፍያዎችን በተመለከተ መመሪያ ያወጣል፤ ያስፈጽማል፤
5. የአደራ ሂሳብ አፈጻጸምን አስመልክቶ መመሪያ አዘጋጅቶ ለጠቅላላ ጉባኤዉ ያቀርባል፤ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
6. ማናቸውም የአደራ ሂሳብ አያያዝና አመራር በትክክል እየተካሄደ መሆኑን ለመቆጣጠር በማናቸውም ጊዜ የኦዲት ምርመራ እንዲካሄድ ሊያደርግ ይችላል፤
7. ከአደራ ሂሳብ አያያዝ ጋር የሚነሱ የደንበኞች ቅሬታዎችን ይቀበላል፣ ማናቸውንም ሰው በማነጋገር ምርምራ ለማድረግ ይችላል፤
8. ከአደራ ሂሳብ ጋር የተያያዘ ሥራን በአግባቡ ያለመወጣት ሁኔታ ሲከሰት ጉዳዩ በሥነ-ምግባር ጉባኤ ታይቶ ውሳኔ እንዲያገኝ ለፍትሕ ቢሮ ሊመራው ይችላል፤
9. ከአደራ ሂሳብ  የሚገኝ ወለድ ወይም ማናቸውም ሌላ ገቢ አጠቃቀምን የሚመለከት መመሪያ ያዘጋጃል፣ በጠቅላላ ጉባኤዉ ሲጸድቅ በተግባር ያውላል፤
10. በዚህ ዓዋጅ ሌሎች አንቀጾች ለማህበሩ የአደራ ሂሳብን አስመልክቶ የተሠጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፤
11. ስለአደራ ሂሳብ ምንነት፣ አያያዝና፣ ሪፖርት አደራረግ እንዲሁም መደረግ ስላለበቸው ጥንቃቄዎች ተገቢው ግንዛቤ እንዲፈጠር ተከታታይ ስልጠናዎችን ይሰጣል ወይም  እንዲሠጡ ያደርጋል፤
12. የደንበኞች ጥቅም መጠበቁን ያረጋግጣል፤እንዲሁም የደንበኞችን ጥቅም ለማስጠበቅ ጠቀሜታ ያላቸው የጠበቃ መብቶች መከበራቸውን ይከታተላል፤
13. ሴት ጠበቆች በወሊድ ምክንያት ከስራ ሲለዩ ደንበኖቻቸዉ ላይ መጉላላት እንዳይደርስ በያዚቸዉ ጉዳይ ላይ ፍርድ ቤቶች ቅድሚያ እንዲሰጡ በየደረጃዉ ካሉ ፍርድ ቤቶች ጋር በቅርበት ይሰራል፤
14. የህግ ትምህርት ጥራት እንዲጠበቅ፤ የህግ የበላይነት እንዲከበር፤ ሰብአዊ መብት እንዲከበር፤ የጥብቅና ሙያ እና አጠቃላይ የኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት እንዲያድግ የበኩሉን አስተዋጽዖ ያደርጋል፤

15. የጥብቅና አገልግሎትን በተመለከተ የሕግ ጥናት በማድረግ የጥናት ውጤቱን ተግባራዊ ያደርጋል፣ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፤
16. የማህበሩ አባላት ይህን አዋጅና  አዋጁን ለማስፈፀም የወጡ ደንቦች እና መመሪያዎችን በማክበር የጥብቅና አገልግሎትን እየሰጡ መሆኑን ይከታተላል፡፡

63. **የጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባራት**

ጠቅላላ ጉባዔው በዚህ አዋጅ መሰረት ፍቃድ የተሰጣቸውን ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች በሙሉ የሚያካትት ሆኖ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የማህበሩን ፕሬዝዳንት እና ምክትል ፕሬዝዳንት ይሾማል፣ ይሽራል፤
2. የማኀበሩን ስታራቴጂክ ዕቅድ፣ ዓመታዊ ዕቅድና በጀት ያጸድቃል፤
3. የአባላትን መዋጮ መጠን ይወስናል፤
4. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን እና የውጪ ኦዲተሮችን ሪፖርት ይመረምራል ያፀድቃል፤
5. ለአባላቱ ጠቅላላ ጥቅም እና ለፍትሕ ተደራሽነት ጠቀሜታ ባላቸው ጉዳዮች ላይ ይወስናል፤
6. የውጭ ኦዲተሮችን ይሾማል፤
7. በሌሎች የማኀበሩ አካላት የሚሰጡ ውሣኔዎች ከሕዝብ ጥቅም እና ከማኀበሩ ዓላማ ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸዉን ያረጋግጣል፤
8. ለማኀበሩ ሌሎች አካላት በግልጽ ባልተሰጡ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፤
9. የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ይሾማል፤
10. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ስልጣኑን በከፊል ለሌላ አካል በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤
11. የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፣ ያሻሽላል፣ያፀድቃል፡፡

64. **የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አቋም፤**

1. ማኀበሩ የአስፈፃሚነት ስልጣን ያለው የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይኖረዋል፤
2. ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሰባት አባላት ይኖሩታል፤
3. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ከጠቅላላ ጉባኤው አባላት መካከል ተመርጠዉ ይሾማሉ፡፡

64. **የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሥልጣንና ተግባራት**

የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1) ማኀበሩን ያስተዳድራል፤

2) የማኀበሩን ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ይጠራል፤

3) የጠቅላላ ጉባዔ ውሣኔዎችን ይፈጽማል ያስፈጽማል፤

4) በጠቅላላ ጉባዔው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፤

5) የሠራተኞችን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፤

6) የሠራተኞችን ደመወዝና አበል ይወስናል፤

7) ፕሬዝዳንቱ እና ምክትል ፕሬዝዳንቱ ሥራቸውን በአግባቡ ማከናወናቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

## 65. የፕሬዝዳንት እና ምክትል ፕሬዝዳንት ስልጣንና ተግባራት

1) ፕሬዝዳንቱ አጠቃላይ የማኀበሩን ሥራ የሚመራ ሆኖ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤዉ እና ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ይሆናል፤

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፕሬዝዳንቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት አሉት፡-

ሀ.ማህበሩን ወክሎ ውል ይዋዋላል፣ይከሳል፣ ይከሰሳል፣ ማህበሩ በሚከስበት፣በሚከሰስበት ወይም በሌላ ተመሳሳይ የህግ ጉዳይ ማህበሩን ወክሎ የሚቀርብ ጠበቃ ይወክላል፣የማህበሩን ጉዳይ ማስፈጸም እንዲችል የማህበሩን ሰራተኛ ወይም ሶስተኛ ወገን እንደአስፈላጊነቱ ይወክላል፤

ለ. የማኀበሩን ዓመታዊ ዕቅድ፣ በጀት፣ የሥራ ክንውን እና የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ያቀርባል፤

ሐ. ስራ የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ረቂቅ ያዘጋጃል፣ በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሲጸድቅ ተግባራዊ ያደርጋል፤

መ. ማኀበሩ የሰው ኃይል አስተዳደር መመሪያ መሠረት የማኀበሩን ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

ሠ. ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የማኀበሩን ስራዎች ያሰራል፤ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር ባለው ግንኙነት ማኀበሩን ይወክላል፤

ረ. ጠቅላላ ጉባዔና የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ውሳኔዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ይከታተላል፤

ሸ. ጠቅላላ ጉባዔውና በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

3) የማህበሩ ምክትል ፕሬዝዳንት፡-

ሀ. ፕሬዝዳንቱ በማይኖሩበት ጊዜ ወይም ሥራውን ሊሰራ በማይችልበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤

ለ. በሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ወይም በፕሬዝዳንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

66. **ዋና ፀሐፊ**

ዋና ፀሐፊው በስራ አስፈፃሚው ኮሚቴ የሚሾም ሆኖ ተጠሪነቱ ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉ እና ለማኅበሩ ፕሬዝዳንት ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት አሉት፡-

1. የማኅበሩን የዕለት ተዕለት ሥራ ይመራል፣ያከናውናል፤
2. የጠቅላላ ጉባኤውና የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ቃለ ጉባኤዎች በአግባቡ መያዛቸውንና መጠበቃቸውን ያረጋግጣል፤
3. ከፕሬዝዳንቱ ጋር በመማከር የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን የስብሰባ አጀንዳ ያዘጋጃል፤
4. ሥራ አስፈፃሚው ኮሚቴ በሌላ ሁኔታ እንዲፈፀም የመወሰን ስልጣኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ፀሐፊው ከሌሎች ሠራተኞች ጋር በመሆን የማኅበሩን የባንክ ሂሣብ ይከፍታል፤ ያንቀሳቅሳል፤
5. የማኅበሩን የንብረት አስተዳደር እና የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት በአግባቡ መዘርጋቱን እና የሂሣብ ሰነዶች በአግባቡ መያዛቸውን ያረጋግጣል፤
6. የማህበሩ ንብረትና ሂሳብ ተቀባይነት ባለው የሂሳብ ዘዴ መያዙን ያረጋግጣል፤
7. ሌሎች በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው እና በፕሬዝዳንቱ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

67. **በማህበሩ ውስጠ-ደንብ ስለሚወሰኑ ጉዳዮች**

ስለ ጠቅላላ ጉባኤው እና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው አመራር አካላት አደረጃጀት፣ ሀላፊነት፤ ስለ ፕሬዝዳንት፣ ምክትል ፕሬዝዳንት እና ሌሎች ሰራተኞች የስራ ድርሻ፣ የምርጫና ስብሰባ ሰነ-ስርዓት፣የማህበሩ ልዩልዩ አካላት የስራ ዘመን  እና ሌሎች ለማህበሩ በህግ የተሰጡ ስልጣንና ተግባራት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ማህበሩ በሚያወጣው ውስጠ-ደንብ ይወሰናሉ፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የጠበቆች አስተዳደር ቦርድ

68. ***መቋቋም***

የጠበቆች አስተዳደር ቦርድ ከዚህ በኋላ “ቦርዱ” እየተባለ የሚጠራዉ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

ቦርዱ በፍትሕ ቢሮ ኃላፊው  አቅራቢነት በክልሉ ፕሬዝዳንት  የሚሾሙ ከሚከተሉት አካላት የተውጣጡ ሰባት አባላት ይኖሩታል፡-

1. ከጠበቆች ማህበር………….. ሁለት፣

2. ከፍትህ ቢሮ ………………ሁለት ሆኖ ዉክልናዉ የፆታ ተዋፅኦን በጠበቀ መልኩ ይሆናል፤

3. ከክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት …….አንድ ዳኛ፣

4. ከክልል ምክር ቤት የፍትህ፣የሰላም እና ዴሞክራታይዜሽን ቋሚ ኮሚቴ…….አንድ ፣

5. ከክልሉ የፍትህ አካላት ስልጠናና ምርምር ኢንስቲትዩት ……..አንድ ተወካይ፤

6. የቦርዱ አባላት የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ሲሆን አንድ አባል ከሁለት የሥራ ዘመን በላይ መመረጥ አይችልም፤

7. የቦርዱ ሰብሳቢ በክልሉ ፍትህ ቢሮ የሚመደብ ሆኖ ጸሀፊ ከቦርዱ አባላት መካከል በአባላቱ ይመረጣል፡፡

69. **የቦርዱ ተግባርና ኃላፊነት፤**

1. በማኅበሩ የሚወሰዱ ዕርምጃዎችና ዉሳኔዎች፤ እንዲሁም በማህበሩ በሚወጡ መመሪያዎች እና ሌሎች ተመሳሳይ ሰነዶች ሕጋዊነት ላይ ቁጥጥር የማድረግ፤

2. በማህበሩ የሚወሰኑ ዉሳኔዎች ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን ተቀበሎ መመርመር እና ዉሳኔ መስጠት፤

3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 75(4) መሰረት የዲሲፕሊን ጉባኤዉ፤ አንቀጽ 77 መሰረት የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና ኮሚቴዉ፤ እንዲሁም በአንቀጽ 81 መሰረት የጥብቅና ፍቃድ ገምጋሚ ኮሚቴ በሚሰጡት ዉሳኔ ላይ የሚቀርብ ቅሬታን ተቀብሎ መመርመር፤ ዉሳኔ መስጠት፤

4. ቅሬታዉን በሚመረምርበት ወቅት ትክክለኛ ዉሳኔ ለመስጠት ይረዳል ብሎ ካመነ አዲስ ማስረጃ አስቀርቦ የማየት፤

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 የተጠቀሱት ኮሚቴዎች ወይም ፍትሕ ቢሮ ወይም ጉባኤዉ በአግባቡ ያላጣራዉ ወይም ያላጤነዉ ፍሬ ነገር ወይም ማስረጃ ካለ ጉዳዩን ዉሳኔ ለሰጠዉ አካል በድጋሚ እንዲታይ ለአንድ ጊዜ መልሶ የመምራት፤

6. ጠበቆች እና የጥብቅና ድርጅቶች ሊይዙት የሚገባውን የሙያ ኃላፊነት መድን መጠን፤ እና የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ መጠንና የአከፋፈል ሥርዓትን በመመሪያ የመወሰን፡፡

70. **ስለ ቦርድ ጽህፈት ቤት እና በጀት**

1. ቦርዱ በፍትህ ቢሮ ዉስጥ ጽህፈት ቤት ይኖረዋል፤

2. የቦርዱ ጽህፈት ቤት ሰራተኞች በፍትሕ ቢሮ ይመደባሉ፤ ጽህፈት ቤቱ የሚሰራዉ ስራ ዝርዝር ቦርዱ በሚያወጣዉ መመሪያ ይወሰናል፤

3. የቦርዱ አባላት የቦርዱን ስራ በሚፈፅሙበት ጊዜ ሊከፈላቸው የሚገባ ክፍያ በፍትህ ቢሮ ይሸፈናል፤

4. ስለቦርዱ በጀት አስተዳደርና ስለቦርድ አባላት ክፍያ ዝርዝሩ በፍትህ ቢሮ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

71. **የቦርድ አሰራር እና ውሳኔ**

1. ቦርዱ በአመት ቢያንስ አራት ጊዜ ይሰበሰባል፣
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ሰብሳቢው በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፣
3. ቦርዱ የአባላቱን መደበኛ ስራ በማይጎዳና የቦርዱን ስራ በማይስተጓጎል መልኩ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤
4. ከቦርዱ አባላት ቢያንስ አምስቱ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፤
5. የቦርዱ ውሳኔ የሚሰጠው በስምምነት ይሆናል ሆኖም ስምምነት ባልተገኘ ጊዜ በስብሰባዉ በተገኙ አባላት አብላጫ ድምጽ ሲደገፍ ይሆናል፤ድምፅ እኩል ለእኩል በተከፈለ ጊዜ የቦርዱ ሰብሳቢ የደገፈው ወገን አሸናፊ ይሆናል፣
6. የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሀኖ ቦርዱ የራሱን የውስጥ አሰራር ስርዓት በተመለከተ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ሳይቃረን በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

72. **በቦርዱ ዉሳኔ ላይ ስለሚቀርብ ይግባኝ**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 70 ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) መሰረት በቦርዱ በሚሰጥ ዉሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን ይግባኙን ዉሳኔዉን ባወቀ በ30 ቀናት ዉስጥ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

74. **በቦርዱ ስለሚመሩ አደረጃጀቶች ተጠሪነት፤**

በዚህ አዋጅ የተቋቋሙት የጠበቆች ዲሲፕሊን ጉባኤ፣ የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና ኮሚቴ እና የጥብቅና ፈቃድ ገምጋሚ ኮሚቴ ተጠሪነት ለቦርዱ ይሆናል፡፡

75. **የጠበቆች ዲስፕሊን ጉባኤ መቋቋምና አወቃቀር፤**

1. የጠበቆች ዲሲፕሊን ጉባኤ ከዚህ በኋላ “ጉባኤው” እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤
2. ጉባኤው ከሚከተሉት አካላት የተውጣጡና በየተቋማቱ ተመርጠው በፍትሕ ቢሮው ኃላፊ የሚሾሙ አምስት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) ከፍትህ ቢሮ............................ሁለት ተወካይ፣

ለ) ከጠበቆች ማህበር .....................ሁለት ተወካይ፣

ሐ) ከክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት...... አንድ ተወካይ፡፡

3. የአንድ አባል የስራ ዘመን ሁለት ዓመት ሲሆን ከሁለት ጊዜ በላይ ሊመረጥ አይችልም፤

4. የጉባኤዉ ሰብሳቢ በፍትህ ቢሮ የሚመደብ ሆኖ የጠበቆች ማህበር የጉባዔዉ ፀሀፊ ይሆናል፡፡ ጉባዔዉ

   ሀ. እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸዉም ጊዜ መሰብሰብ ይችላል፣

   ለ. ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል፣

   ሐ. ዉሳኔዎችን በድምጽ ብልጫ ያሳልፋል፤ ሆኖም ድምጽ እኩል ሲሆን በሰብሳቢዉ በኩል ያለዉ ድምጽ የጉባኤው ዉሳኔ ሆኖ ይጸድቃል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ከ (ሀ)-(ሐ) የተደነገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጉባኤዉ የራሱን የስብሰባ ስነ-ስርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

75. **የጠበቆች ዲስፕሊን ጉባኤ ተግባርና እና ኃላፊነት፤**

1. የጠበቆችና የጥብቅና ድርጅቶች የሥራ አፈጻጸም ከሙያ ሥነ ምግባር ደንብ ጋር የተጣጠመ መሆኑን መከታተል የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤
2. ይህንን አዋጅ ወይም የጠበቆች የስነ-ምግባር ደንብ ወይም መመሪያ በመተላለፍ በጠበቃ እና ጥብቅና ድርጅት ላይ የሚቀርብ ክስን ይመረምራል፤ ክሱ ጠበቃዉን ወይም የጥብቅና ድርጅቱን የሚያስቀርብ መሆን አለመሆኑን ይወስናል፤
3. ክሱ እና ማስረጃዉ ጠበቃዉን የሚያስቀርብ መሆኑን ከወሰነ ጠበቃዉ መልሱን በ30 ቀናት ዉስጥ በጽሁፍ እንዲያቀርብ በመጥሪያ ላይ በመግለጽ ክሱን ለጠበቃዉ ይልካል፤
4. በጠበቃዉ ላይ የቀርበዉን ክስ እና ማስረጃ፤ እንዲሁም በጠበቃዉ በኩል የተሰጠ መልስ እና ማስረጃ ከመረመረ እና ካከራከረ በኋላ ዉሳኔ ይሰጣል፤
5. የጠበቆች ስነ-ምግባር ብቃት የሚጎለብትበትን፤ የጥብቅና ሙያ ክብር የሚጠበቅበትን ሁኔታ እያጠና ለቦርዱ ሀሳብ ያቀርባል፡፡
6. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በዚህ አዋጅ የተሰጠውን የድስፕሊን ክስ የማየት ስልጣን ለዞን ወይም ለወረዳ የጠበቆች ድስፕሊን ኮሚቴ በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤ ውክልናውም ምክንያቱ ተገልጾ በጽሁፍ መሰጠት አለበት፤

76. **የዞን ወይም የወረዳ የጠበቆች ድስፕሊን ኮሚቴ**

   1. ኮሚቴው ከክልሉ የጠበቆች ድስፕሊን ጉባኤ በውክልና ለሚሰጠው የጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የድስፕሊን ጉዳይን ለማየት የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

1. የፍትህ መምሪያው ወይም ጽህፈት ቤት ሃላፊ እንደ ቅደም ተከተላቸዉ… ሰብሳቢ

2. ከጠበቆች ማኅበር የሚወከሉ ሁለት ……………………………………… አባል
3. ከፍትህ መምሪያው ወይም ጽ/ቤቱ የሚወከል አንድ ተወካይ…………………አባል
4. ከከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚወከል አንድ ተወካይ………………………………አባል

2. የኮሚቴው ሰባሳቢና ጸሀፊ፣ የአንድ አባል የሥራ ዘመን እና የጉባኤው አሰራርና ውሳኔ በዚህ አዋጅ ለክልሉ የጠበቆች ድስፕሊን ጉባኤ በተደነገገው መሰረት ይሆናል፡፡

**77. የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና ኮሚቴ መቋቋምና አወቃቀር**

1. የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና ኮሚቴ ከዚህ በኂላ "የፈተና ኮሚቴ" እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤
2. የፈተና ኮሚቴው ከሚከተሉት አካላት የተውጣጡ በየተቋማቱ የሚመረጡና በፍትሕ ቢሮው ኃላፊ የሚሾሙ ሰባት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ. ከፍትህ ቢሮ ……………………ሁለት፤

ለ. ከጠበቆች ማህበር ……………..ሁለት፣

ሐ. ከክልሉ  የፍትህ አካላት ስልጠናና የህግ ምርምር እንስቲትዩት ………..አንድ

መ. በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት  ……………አንድ፣

ሠ. ከአሶሳ ዩኒቨርስቲ ህግ ትምህርት ቤት …………አንድ ተወካይ፡፡

3. የአንድ የፈተና ኮሚቴ አባል የስራ ዘመን ሁለት አመት ሲሆን ከሁለት ጊዜ በላይ በፈተና ኮሚቴ አባልነት ሊመረጥ አይችልም፤

4. የፈተና ኮሚቴዉ ሰብሳቢ በፍትህ ቢሮ በኩል የሚመደብ ሆኖ የጉባዔዉ ፀሀፊ ከአባላቱ ውስጥ አባላት የሚመረጥ ይሆናል፤

5. የፈተና ኮሚቴዉን ስብሰባ በተመለከተ፡-

ሀ. ኮሚቴዉ እንደ አስፈላጊነቱ በማንኛውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፣

ለ. ከኮሚቴዉ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል፣

ሐ. የኮሚቴዉ ዉሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም  ድምጽ እኩል በእኩል ከተከፈለ የሰብሳቢው ድምጽ ወሳኝነት ይኖረዋል፡፡

**78. የኮሚቴው ተግባርና እና ኃላፊነት፤፡-**

1. በፍትሕ ቢሮው የጥብቅና ፍቃድ ከሚሰጠው የስራ ክፍል ጋር በመመካከር ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ የጥብቅና ችሎታ መመዘኛ ፈተና እያዘጋጀ በተወሰነ ጊዜ እና ቦታ ለአመልካቾች ይሰጣል፤
2. የፈተናውን ስነ-ስርአትና ጊዜ ይወስናል
3. የፈተና ወረቀቶችን ያርማል፤ ለማለፊያ የሚያበቃ ነጥብ ይወስናል፤ ዉጤቱን በይፋ ያስታዉቃል፤

4. ፈተናዉን በስኬት ላጠናቀቀ ተፈታኝ ፈተናዉን ማለፉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ይሰጣል፤
5. የፈተና ስነ-ስርዐት ደንብ አዘጋጅቶ ለቦርዱ አቅርቦ ሲጸድቅ በስራ ላይ ያዉላል፡፡

**79. የኮሚቴው አባላት ውሎ አበል**

የኮሚቴው አባላት የኮሚቴውን ሥራ በሚፈጸሙበት ጊዜ ሊከፈላቸው የሚገባ ክፍያ በፍትሕ ቢሮው ይሸፈናል፡፡

80. **የጥብቅና ፍቃድ ገምጋሚ ኮሚቴ መቋቋምና አወቃቀር**

1. ለአመልካቾች የጥብቅና ፈቃድ ሊሰጥ የሚገባው ስለመሆን አለመሆኑ የሚወስን የጥብቅና ፍቃድ ገምጋሚ ኮሚቴ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፣
2. ኮሚቴዉ ከሚከተሉት አካላት የተውጣጡ በየተቋማቱ የተመረጡ  አምስት አባላት ይኖሩታል፡-
   ሀ. ከፍትህ ቢሮ ………………ሁለት ተወካዮች/የፆታ ተዋፅኦን የጠበቀ)፣
   ለ. ከጠበቆች ማህበር ………..ሁለት ተወካዮች፣ እና
   ሐ. በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት………. አንድ ተወካይ፡፡
3. የአንድ አባል የስራ ዘመን ሁለት አመት ሲሆን ከሁለት ጊዜ በላይ በአባልነት ሊመረጥ አይችልም፤
4. የኮሚቴዉ ሰብሳቢ ከአባላቱ መካከል በፍትሕ ቢሮው ኃላፊ የሚሰየም ይሆናል፡፡

**81. የጥብቅና ፍቃድ ገምጋሚ ኮሚቴዉ ተግባርና እና ኃላፊነት**

1. የአመልካቹን ማስረጃዎች መርምሮ አመልካቹ ፍቃድ እንዲሰጠዉ ወይም እንዳይሰጠዉ ይወስናል፤
2. አመልካቹ ለፍትህ ስራ አካሄድ የሚስማማ የስነ-ምግባር ብቃት ያለዉ መሆኑን ለማረጋገጥ ማንኛዉንም ሰዉ መጠየቅ ወይም ማስረጃ አስቀርቦ መመርመር ይችላል፡፡

**82. የጥብቅና ፍቃድ ገምጋሚ ኮሚቴዉ ስብሰባ**

1. ኮሚቴዉ እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸዉም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፤
2. ከኮሚቴዉ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፤
3. የኮሚቴዉ ውሳኔዎች በስብሰባዉ በተገኙ አባላት በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢዉ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፤
4. በዚህ አንቀጽ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚቴዉ የራሱን የስብሰባ ስነስርአት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሶስት

## ስለ ፍትህ ቢሮ

### 83. የፍትህ ቢሮ ተግባርና እና ኃላፊነት

1. የጥብቅና ፍቃድ ገምጋሚ ኮሚቴ የጥብቅና ፈቃድ እንዲሰጠው ለወሰነለት ባለሙያ የጥብቅና ፍቃድ ይሰጣል፤
2. ጠበቆችን፤ የጥብቅና ድርጅቶችን እና ከጠበቃ እና ከጥብቅና -ድርጅቶች ጋር የሚሰሩ ሰዎችን ይመዘግባል፣ የጥብቅና ፍቃድ ያድሳል፣
3. የጠበቆች ዲስፕሊን ጉባኤ በሚወስነዉ መሰረት የጥብቅና ፍቃድ ያግዳል፣ይሰርዛል፤
4. በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ ደንብ በሚወሰነው መሰረት ለሚሰጠው የጥብቅና ፍቃድና ሌሎች አገልግሎቶች ክፍያ ይሰበስባል፤
5. በጠበቆችና በጥብቅና ድርጅቶች ለሚሰጡ የሕግ አገልግሎቶች ከቦርዱ እና ከማህበሩ ጋር በመመካከር መለኪያዎችን ያወጣል፤
6. የስነ ምግባር ጥሰት ፈጽሟል ተብሎ ጥቆማ በቀረበበት ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ላይ የስነ-ምግባር ጥሰቱ ስለመፈፀሙ ለማረጋገጥ ምርመራ ያካሂዳል፣ የዲስፕሊን ክስ ይመሰርታል፤ ይከራከራል፤
7. በዚህ አዋጅ እና ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጡ ደንብና መመሪያዎች የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት በሙሉ ወይም በከፊል ለጠበቆች ማህበር በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፤
8. የጥብቅና ማህበሩ እንዲጠናከር ለማድረግ የተለያዩ አደረጃጀቶች እና ኮሚቴዎች እንዲቋቋሙ ድጋፍ ያደርጋል፤ ማህበሩ ከሌሎች ተቋማት ጋር ህጋዊ ግንኙነት ስለሚፈጠርበት ሁኔታ ያመቻቻል፤
9. አዋጁን ለማስፈጸም በማህበሩ እና በቦርዱ የሚወጡ መመሪያዎችን በማዘጋጀት እና እንዲጸድቁ በማድረግ፤ እንዲሁም አጠቃላይ የጥብቅና አገልግሎትን በተመለከተ በማህበሩ፤ በቦርዱ ወይም ሌሎች በሚመለከታቸዉ አካላት የሚነሱ አዲስ ህግ እንዲወጣ ወይም የህግ ማሻሻያ እንዲደረግ በሚያስፈልጉ ሀሳቦች ላይ እንደአግባብነቱ የህግ ረቂቅ በማዘጋጀት እና በሚመለከተዉ አካል እንዲጸድቅ በማድረግ አስፈላጊዉን እገዛ ያደርጋል፤

10. ማህበሩ በሰለጠነ የሰዉ ሀይል እንዲደራጅ፣ ለመነሻ የሚሆን በጀት እንዲኖረዉ እና እንደተቋም ለመንቀሳቀስ እንዲችል አስፈላጊዉን ድጋፍ ያደርጋል፤

11. ሌሎች በዚህ አዋጅ፣ ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸዉ ህጎች የተሰጡትን ስልጣን እና ተግባራት ይፈጽማል፡፡

## ክፍል ስድስት

## የዲሲፕሊን ጥፋቶች እና እርምጃዎች

### ንዑስ ክፍል አንድ

### ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋት እና ቅጣት

**84. ቀላል የዲሲፒሊን ጥፋት አይነቶች፤**

የሚከተሉትና መሰል በጠበቆች ስነ-ምግባር ደንብ የተደነገጉ በጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የሚፈፀሙ ጥፋቶች ቀላል የዲሲፒሊን ጥፋቶች ናቸዉ፡-

1. የጥብቅና ፍቃድን ለደንበኛ፤ለፍርድ ቤት ወይም ለሚመለከተዉ አካል እንዲያሳይ በተጠየቀ ጊዜ ለማየሳት ፈቃደኛ ያለመሆን፤
2. በፍርድ ቤት ወይም መሰል ተቋማት የሙያ ባልደረባን መዝለፍ፣ ማንቋሸሽ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ ክብሩን ለመቀነስ መሞከር፤
3. በጠበቃ ያልተወከለ ተከራካሪ ባጋጠመው ጊዜ ሆን ብሎ ይህንኑ ተከራካሪ ወገን ሊያሳስቱ የሚችሉ ድርጊቶች መፈጸም፤
4. ለጠበቆች ማህበር መክፈል የሚጠበቅበትን ክፍያ ወይም መዋጮ በተደጋጋሚ እና በወቅቱ ያለመክፈል፤
5. የጥብቅና ፍቃድን በወቅቱ አለማሳደስ፣
6. ባልታደሰ የጥብቅና ፈቃድ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት፡፡
7. የጥብቅና ፍቃዱን ለጥብቅና ፍቃድ ሰጭው ተቋም ሳይመልስ በሌላ ቋሚ ስራ ተሰማርቶ መገኘት፤

**85. የቀላል የዲስፒሊን ጥፋት ቅጣት**

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 84 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ከተደነገጉ ጥፋቶች አንዱን የፈፀመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የቃል ማስጠንቀቂያ በዲሲፒሊን ጉባኤው ይሰጠዋል፤ ለሁለት ጊዜ የቃል ማስጠንቀቂያ የተሰጠዉ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ለሶስተኛ ጊዜ ተመሳሳይ ጥፋት ከፈጸመ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 84 ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) የተደነገጉትን ጥፋቶች የፈፀመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤

3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 84 ንዑስ አንቀፅ (5)-(7)፣) የተደነገጉትን ጥፋቶች የፈፀመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት እንደነገሩ ሁኔታ ከብር አምስት ሽ እስከ ብር ሰባት ሽህ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## ከባድ የዲሲፒሊን ጥፋት እና ቅጣት

### 86. ከባድ የዲሲፒሊን ጥፋት አይነቶች

የሚከተሉት እና መሰል በጠበቆች ስነ-ምግባር ደንብ የሚጠቀሱ በጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የሚፈፀሙ ጥፋቶች ከባድ የዲሲፒሊን ጥፋቶች ናቸዉ፡-

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 18(3) ስር የተዘረዘሩ ሰዎችን በጠበቃ ረዳትነት ወይም በህግ ጉዳይ ጸሀፊነት መቅጠር እና ማሰራት፤
2. በስሩ የቀጠራቸውን የጠበቃ ረዳትና ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች ለፍቃድ ሰጭው አካል ያለማሳወቅና ያለማስመዝገብ፤
3. ያለበቂና አሳማኝ ምክንያት ተለዋጭ ቀጠሮ በተደጋጋሚ መጠየቅና የፍርድ ቤት ጉዳይ እንዲጓተት ማድረግ፤
4. እሱ ከሚወክለዉ ደንበኛ ጠበቃ ጋር በችሎት ወቅትም ሆነ ከችሎት ዉጭ መዘለፍ፤ ማንቋሸሽ፤ማመናጨቅና መሰል ያልተገባ ባህሪ ማሳዬት፤
5. ያለበቂና አሳማኝ ምክንያት በቀጠሮ ቀን ፍርድ ቤት ያለመገኘት፣
6. የጥብቅና አገልግሎት መስጫ ቢሮ ሳይኖር የጥብቅና አገልግሎት መስጠት፤
7. በህግ ከተፈቀደው ምክንያት ውጭ ተከታታይ የግዴታ የህግ ስልጠና በአግባቡ አለመውሰድ፤
8. የደንበኛን ሚስጥር አለመጠበቅ፤
9. ጉዳዩ ያለበትን ሁኔታና የደረሰበትን ደረጃ በደንበኛው ሲጠየቅ በአግባቡ ያለማሳወቅ፣ ደንበኛን ማመናጨቅ ወይም ክብሩን መንካት፤
10. ነፃ የጥብቅና አገልግሎት እንዲሰጥ በሚመለከተዉ አካል ሲመራለት ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆን፤
11. የጥብቅና ስራን በአገናኝ አማካኝነት መስራት ወይም ለሌሎች ጠበቆች የአገናኝነት ስራ መስራት፤
12. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 23(1) ላይ ከተደነገገዉ በስተቀር ከደንበኛ ጋር የሚደረግ የጥብቅና አገልግሎት ውል ስምምነትን በፅሁፍ ያለማድረግ፤

13. ያለበቂ ምክንያት የጥብቅና ውልን ማቋረጥ ወይም በጥብቅና ውሉ ከተገለፀው የጥብቅና አገልግሎት ክፍያ በተጨማሪ ከደንበኛው ፍላጎት ውጪ ያለበቂ ምክንያት ተጨማሪ ክፍያ መቀበል፤
14. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 33 በተጠቀሰዉ ጊዜ ዉስጥ የመድን ዋስትና ሳይገባ ወይም የመድን ዋስትናው በወቅቱ ሳይታደስ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት፤
15. በፍርድ ቤት ወይም ሌሎች ውሳኔ በሚሰጡ አካላት ዘንድ የሚታዩ ጉዳዮችን በተመለከተ አግባብ ባልሆነ መንገድ ውሳኔ ለማግኘት መጣር፣
16. የጥቅም ግጭት የሚያስነሳ ወይም የጥቅም ግጭት ያለበት ጉዳይ መሆኑን እያወቀ ጉዳዩን መያዝ፤
17. ከተሰጠው የጥብቅና ፍቃድ ደረጃ በላይ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት፤
18. የደንበኛውን ማስረጃ በአግባቡ ለፍርድ ቤት አለማቅረብና ከአቅም በታች በመከራከር መዝገቡ ውጤታማ እንዳይሆን ማድረግ፤
19. የጥብቅና ፍቃድን በማንኛውም ሁኔታ ለሶስተኛ ወገን መጠቀሚያ አሳልፎ መስጠት፤
20. ነፃ የጥብቅና አገልግሎት የመስጠት ግዴታውን እያወቀ ወይም በቸልተኝነት በአግባቡ ባለመወጣት የደንበኛን ጉዳይ እንዲበላሽ ወይም ውጤታማ እንዳይሆን ማድረግ፤
21. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 35 እና 36(1)፣(4) እና (5) የተደነገጉትን ግዴታዎች በመተላለፍ ከደንበኛ የአደራ ሂሳብ አያያዝ ጋር የተያያዙ ጥፋቶችን መፈፀም፤
22. ከተቃራኒ ባለጉዳይ ጠበቃ ጋር በመመሳጠር ወይም ማስረጃ በማጥፋት የደንበኛ ጉዳይ ውጤታማ እንዳይሆን ማድረግ፤
23. የህግ መሰረት የሌለውንና እንደማያዋጣ በግልጽ የሚታወቅ ጉዳይ ያዋጣል በማለት መያዝና ከደንበኛ ክፍያ መቀበል፤
24. ሐሰተኛ ማስረጃ በመጠቀም ወይም በማንኛውም ሁኔታ በማታለል የጥብቅና ፍቃድ ማውጣት፤
25. ከጥብቅና ሙያ አገልግሎት ጋር በተያያዘ በእምነት ማጉደል፣ ማታለል፣ ማጭበርበር፣ ሀሰተኛ ሰነድ ማዘጋጀት ወይም መገልገል፣ስርቆት፣ እና በመሳሰሉት ከስነ ምግባር ጉድለት ጋር በተያያዙ ወንጀሎች በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣት፤
26. ከጥብቅና ሙያ አገልግሎት ጋር በተያያዘ ሐሰተኛ ማስረጃ ማቅረብ ወይም እንዲቀርብ ማድረግ፣ ሀሰተኛ ምስክር በማዘጋጀት በሀሰት ማስመስከር፣ተከሳሽ ፍርድ

ቤት እንዳይቀርብ ወይም እንዲጠፋ ማድረግ ወይም መምከር፣ ለተቃራኒ ወገን ጠቃሚ የሆነን ማስረጃ እንዳይጠቀምበት በማሰብ ማጥፋትና ፍትህ እንዲዛባ በማድረግ እና በመሳሰሉት ከስነ-ምግባር ጉድለት ጋር በተያያዙ ወንጀሎች በፍርድ ቤት ጥፋተኛ ተብሎ መቀጣት፤

27. በታገደ ወይም በተሰረዘ የጥብቅና ፍቃድ መታገዱን ወይም መሰረዙን እያወቀ የጥብቅና አገልግሎት መስጠት፡፡

## 87. የከባድ የዲስፕሊን ጥፋት ቅጣት

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 86 ከንዑስ አንቀጽ (3) - (6) ባሉ ቀላል የዲሲፕሊን ጥፋቶች በዓመት ከሁለት ጊዜ በላይ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 86 ከንዑስ አንቀጽ (1)_(7) ከተዘረዘሩት ጥፋቶች አንዱን የፈፀመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ከብር ሰባት ሺህ አምስት መቶ እስከ ብር አስራ አምስት ሺህ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤
2. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 86 ከንዑስ አንቀጽ (8)-(13) ከተዘረዘሩት ጥፋቶች አንዱን የፈፀመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ከብር ሃያ ሺህ እስከ ብር ሰላሳ ሺህ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤
3. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 86 ከንዑስ አንቀጽ (14)-(20) ከተዘረዘሩት ጥፋቶች አንዱን የፈፀመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት እንደነገሩ ሁኔታ እስከ ስድስት ወር ለሚደርስ ጊዜ የጥብቅና ፈቃዱ ወይም የምዝገባ ምስክር ሰርተፊኬቱ ይታገዳል፤
4. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 86 ከንዑስ አንቀጽ (21)-(27) ከተጠቀሱት ጥፋቶች አንዱን የፈፀመ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የጥብቅና ፍቃዱ ወይም የምዝገባ ሰርተፊኬቱ ይሰረዛል፤
5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 ላይ የተጠቀሱትን ጥፋቶች ፈጽሞ በሶስት አመት ጊዜ ዉስጥ ለሁለት ጊዜ የተቀጣ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ሌላ ተመሳሳይ ከባድ የዲስፕሊን ጥፋት የፈጸመ እንደሆነ የጥብቅና ፍቃዱ ወይም የምዝገባ ሰርተፍኬቱ ከ 6 ወር እስከ 1 አመት ለሚደርስ ጊዜ ሊታገድ ይችላል፤
6. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 3 እስከ 4 ስር የተጠቀሰዉን ቅጣት በአምስት አመት ውስጥ ለሁለት ጊዜ የተቀጣ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት ሌላ ተመሳሳይ ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ፈጽሞ ከተገኘ የጥብቅና ፍቃዱ ወይም የምዝገባ ሰርተፍኬቱ የሚሰረዝ ይሆናል፤
7. በዲሲፕሊን ጥፋተኛ ሆኖ መገኘትና መቀጣት በወንጀል የሚያስጠይቁ የዲሲፕሊን ጥፋቶችን በተመለከተ የወንጀል ተጠያቂነትን አያስቀርም፡፡

## ንዑስ ክፍል ሶስት

## ስለዲሲፕሊን ክስ አቀራረብ፣ ይርጋ፣ ይግባኝ እና የወንጀል ቅጣት

### 88. ስለዲሲፕሊን ክስ አቀራረብና ይርጋ

1. የዲስፕሊን ክስ አቀራረብ እና የክርክር ስነስርአት ቦርዱ በሚያወጣዉ መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፤
2. በቀላል የዲሲፕሊን ጥፋት ላይ የሚቀርብ ክስ የዲሲፕሊን ጥፋቱ በተፈፀመ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፤
3. በከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ላይ የሚቀርብ ክስ የዲሲፕሊን ጥፋቱ በተፈፀመ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ ይታገዳል፡፡

### 89. ስለ ይግባኝ

1. በዲሲፕሊን ጉባኤው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን የዲሲፕሊን ጉባኤው ውሳኔ ግልባጭ በደረሰዉ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፤
2. የይግባኝ ክርክር ሂደት በመደበኛው የወንጀል ይግባኝ አቀራረብ ስርዓት አግባብ ይመራል፤
3. በቦርዱ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን የቦርዱ የውሳኔ ግልባጭ በደረሰው በሰላሳ ቀናት ወስጥ ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

### 90. የወንጀል ተጠያቂነት

በዚህ አዋጅ መሰረት የሚያስቀጡ የዲሲፕሊን ጥፋቶች የወንጀል ድንጋጌዎችን ፍሬ ነገሮች የሚያሟሉ ከሆነ ጠበቃው ወይም የጥብቅና ድርጅቱ አግባብ ባለዉ የወንጀል ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ንዑስ ክፍል አራት

## ስለ መሰየም

### 91. የመሰየም አቤቱታ አቀራረብ

1. በዚህ አዋጅና በአዋጁ መሠረት በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት በከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት የተቀጣ ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የጥፋተኛነት ሪከርድ እንዲሰረዝለትና ስሙ እንዲመለስለት መጠየቅ ይችላል፤
2. የመሰየም አቤቱታ የሚቀርበው ለዲሲፕሊን ጉባኤ ሆኖ አቤቱታው ሊቀርብ የሚችለው ቅጣቱን ከጨረሰ ከሁለት ዓመት በኋላ ነው፡፡

## 92. የመሰየም ሥርዓት

1. አመልካች ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የመሰየም አቤቱታውን ለዲሲፕሊን ጉባኤው ያቀርባል፤
2. የዲሲፕሊን ጉባኤውም አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ለፍትህ ቢሮ ወይም ሌላ የሚመለከተው አካል በአቤቱታው ላይ አስተያየት እንዲሰጥ ያደርጋል፤
3. የዲሲፕሊን ጉባኤውም  የፍትህ ቢሮውን ወይም የሚመለከተውን አካል አስተያየት ከተቀበለና አመልካቹን በአካል በማነጋገር አስፈላጊውን ምርመራ ካደረገ በኋላ ጥፋቱ ከሪከርድ እንዲሰረዝ ሊወስን ይችላል፡፡

## 93. የመሰየም ውጤቶች

1. አመልካቹ የጥፋተኛነት ሪከርድ ይሰረዝለታል፤
2. ሪከርዱ በማናቸውም አይነት ውሣኔ ላይ አይጠቀስም፤ ፍቃዱ ተሰርዞበት ከሆነ ለደረጃዉ የሚሰጠዉን ፈተና ተፈትኖ ካለፈ እና በዚህ አዋጅ የተጠቀሱትን መስፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ ፍቃዱ ይመለስለታል፤
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ድንጋጌ ቢኖርም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 86  (21) - (24) ስር በተደነገጉት ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶች ምክንያት የጥብቅና ፍቃዱ የተሰረዘበት ወይም በእነዚሁ ድርጊቶች በወንጀል የተቀጣ፤ ወይም ከሚሰጠው የጥብቅና አገልግሎት ጋር በተያያዘ በሙስና ወንጀል የተቀጣ፤ ወይም ታስቦ በሚፈጸም እና ከአስር ዓመት ጽኑ እስራት በላይ በሚያስቀጣ ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ የተቀጣ ማንኛውም ጠበቃ ወይም የጥብቅና ድርጅት የተሰየመ ቢሆንም የጥብቅና ፍቃዱ አይመለስለትም፣ በጥብቅና አገልግሎት ሙያ ድጋሚ መሰማራት አይችልም፡፡

## 94. የዲሲፕሊን ጉባኤው ስለሚሰጣቸው ትዕዛዞች

የዲሲፕሊን ጉባኤው አንድ ጠበቃ እንዲሰየም ሲወስን ጠበቃው ጉባኤው ለሚወስነው ጊዜ ያህል ነፃ የማህበረሰብ አገልገሎት እንዲሁም ጉባኤው ለሚወስናቸው ጉዳዮች መጠን ያህል ነፃ የሕግ አገልግሎት እንዲሰጥ ሊያዝ ይችላል፤

## 95. የተፈፃሚነት ወሰን

መሰየምን የሚመለከቱ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ለተቀጡ ጠበቆችም ተፈጻሚ ይሆናል፤

## 96. መሰየምና ቀላል ጥፋቶች

በቀላል ጥፋት የተቀጣ ጠበቃ የመሰየም አቤቱታ ማቅረብ ሳያስፈልገው ቅጣቱን ከጨረሰ አንድ ዓመት በኋላ ሪከርዱ ይሰረዝለታል ወይም ቀሪ ይደረግለታል፤

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 97. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. የክልሉ መስተዳድር ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፤
2. ፍትሕ ቢሮ ቦርዱ እና ማህበሩ በዚህ አዋጅ የተሰጣቸዉን ተግባርና ኃላፊነት ለማስፈጸም የሚያስችላቸውን መመሪያ ሊያወጡ ይችላሉ፤

### 98. መሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

1. ቦርዱ እና ማህበሩ በዚህ አዋጅ መሰረት የተሰጣቸዉን ተግባር እና ሀላፊነት በሁለት አመት ዉስጥ ይረከባሉ፤
2. ቦርዱ እና ማህበሩ ሀላፊነታቸዉን እስኪረከቡ ድረስ ፍትህ ቢሮ የጥብቅና ፍቃድ አሰጣጥ እና አስተዳደር ስራን ይከታተላል፤ይቆጣጠራል፤ያስተዳድራል፤
3. በዚህ አዋጅ ለቦርዱ ተጠሪ የሆኑትን የጥብቅና ሙያ መግቢያ ፈተና ኮሚቴ እና የጠበቆች ዲስፕሊን ጉባኤ ተጠሪነት ማህበሩ እነዚህ ሀላፊነቶች ለመረከብ ብቁ መሆኑን ቦርዱ ሲወስን በአምስት አመት ግዜ ዉስጥ ሁለቱንም ወይም ከሁለቱ አንዱን ወደ ማህበሩ ያስተላልፋል።ፍትሕ ቢሮው ማህበሩ እነዚህን ሀላፊነቶች በአግባቡ ስለመወጣቱ ይከታተላል፣ አስፈላጊ ነው ብሎ ያሰበውን እርምጃ ይወስዳል ወይም የሚመለከተው አካል እንዲወሰድ ያደርጋል፤
4. በዚህ አዋጅ ለቦርዱ ተጠሪ የሆነውን የጥብቅና ፈቃድ ገምጋሚ ኮሚቴ ማህበሩ ይህንን ሀላፊነት ለመወጣት ብቁ በሚሆንበት ጊዜ ተጠሪነቱ ለማህበሩ እንዲተላለፍ ቦርዱ በማንኛውም ጊዜ ሊወስንና ሊያስተላልፍ ይችላል፣
5. ማህበሩ ተደራጅቶ እና ሀላፊነቶቹን መረከብ እንደሚችል ፍትህ ቢሮ ሲያረጋግጥ ሀላፊነቶቹን ሁሉንም ወይም የተወሰኑትን መመሪያ በማውጣት ወደ ማህበሩ ሊያስተላልፍ ይችላል። ፍትህ ቢሮ እነዚህን ሀላፊነቶችን ካስተላለፈ በኋላ ተግባራቱ በአግባቡ ስለመፈጸማቸዉ መከታተል እና ኦዲት የማድረግ እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ አስፈላጊውን እርምጃ ሊወስድ ወይም እንዲወሰድ የማድረግ ሀላፊነት አለበት፣
6. ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ጸንተው በነበሩት ህጎች መሠረት ውሣኔ ያገኛሉ፤

7. ይህ አዋጅ ከመፅናቱ በፊት የተሰጡ የጥብቅና ፈቃዶች በዚህ አዋጅ መሰረት መታደስ ያለባቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የፀኑ ናቸው፡፡

**99. የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች**

1. በክልሉ ፍርድ ቤቶች ስለሚሰሩ ጠበቆችና የግል የህግ ጉዳይ ጸሀፊዎች ፈቃድ አሰጣጥ እና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 151/2010 ዓ/ም በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡
2. ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ህግ ወይም ማናቸዉም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**100. ተፈፃሚነታቸው ስለሚቀጥል ሕጎችና የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች፤**

1. በክልሉ ፍርድ ቤቶች ጠበቆች ፍቃድ አሰጣጥ እና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 151/2010 መሰረት የወጡ ደንብ እና መመሪያዎች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረኑ እና በሌላ ደንብና መመሪያ እስከሚተኩ ድረስ ተፈፃሚነታቸው ይቀጥላል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተጠቀሱት ደንብ እና መመሪያዎች እስከሚሻሻሉ ወይም እስከሚሻሩ ድረስ እንደ አግባብነታቸዉ በጥብቅና ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

101. **አዋጁን ስለማሻሻል፣**

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ሊያሻለዉ ይችላል፤

102. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ፣**

ይህ አዋጅ በክልሉ ልሳነ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አሶሳ፣ የካቲት 28 ቀን 2015 ዓ.ም

አሻደሊ ሀሰን አልአጀብ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት

ፕሬዝዳንት